# ቴቄል (ዳን 5 ፥ 27)

## ክፍል ሁለት

### (ከመቶ በላይ ጥያቄዎች ለሙስሊሞች)

* ገሃነም መጣል የሚሻ አንድ ሙስሊም እንኳ አይኖርም
* ቁርዓን የክርስቶስን ☞ አምላክነት
  ☞ መሢሕነትና
  ☞ አዳኝነት ያረጋግጣል
* ሙስሊሞች በፍቅር የሚያነቡትና ለታላቅ ውሳኔ የሚበቁበትን እውነት የያዘ መጽሐፍ
* ክርስቲያኖች ስለ ቁርአን ሊረዱትና ሙስሊሞችን ሊረዱበት የሚችሉበት ድንቅ መጽሐፍ

አዘጋጅ መምህር ገብረ እግዚአብሔር መኩሪያ

ጥር 2001

www.ethiopianorthodox.org

የቁርዓን መውረድ ዓላማ ታዲያ በአንድ አምላክ ለሚያምኑ አይሁዶችና ክርስቲያኖች ምን ረብ አለው? ሐዲስ ኪዳን የብሉይ ኪዳን ፍፃሜ ቢሆንም ታላቅ ከሆነ አዲስ መገለጥ ጋር ነው የመጣው ቁርአን ግን አዲስ መገለጥ ካላመጣ ቀድሞ እሱ አላህ ያወረዳቸውን መጻሕፍት ማረጋገጥ ለምን አስፈለገ? አላህ በየጊዜው ነቢይ እየላከ መጽሐፍ እያወረደ የቀድሞውን ማረጋገጥ ካለበት አሁንም ቁርአኑን ለማረጋገጥ ሌላ መልዕክትና መልክተኛ መላክ ያስፈልገዋል ነገር ግን ከመሐመድ ድንገተኛ ሞት በኋላ ሌላ አረጋጋጭ ሳይነሳ ብዙ ዘመናት አልፈዋል::

በ7ኛው መቶ ክ/ዘመን የተነሳው መሐመድ ቁርአን ለኔ የወረደው ኦሪትና ወንጌል ትክክለኛ የእግዚአብሔር ቃል መሆናቸውን ለማረጋገጥ ነው ማለቱ ለኛ ጠቃሚ ምስክርነት ነው መጽሐፍ ቅዱስ ግን በራሱ ፍጹምና ምሉዕ ስለሆነ የቁርአንን ድጋፍ የሚሻ አይደለም ነገር ግን ምስክርነቱ -

- በርሱ ዘመን ኦሪትና ወንጌል መኖራቸውንና አገልግሎት ላይ ይውሉ እንደነበር
- ቃሎቹም ንጹህና ያልተበረዙ የማንም ቃል ሳይሆን ከርሱ የወረዱ መሆናቸውን ስለሚያረጋግጥ ነው::

በርግጥም ቁርአኑ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛነት ከዚህም የማያንሱ ሌሎች ምስክርነቶችንም ይሰጣል ለምሳሌ አል-በቀራህ 2 ፥ 21 *«እነዚያ መጽሐፉን የሰጠናቸው ተገቢ ንባቡን ያነቡታል»* በዚህ አንቀጽ በመሐመድ ዘመን መጽሐፍ ቅዱስ ምሉዕ ሆኖ በሚገባ ይነበብና ይታመን እንደነበር ያስረዳል::



አል-ማኢዳህ 5 ፥ 44 *«እኛ ተውራትን በውስጥዋ መምሪያና ብርሃን ያለባት ስትሆን አወረድን እነዚያ ትዛዝን የተቀበሉት ነቢያት በነዚያ ይሁዳውያን በሆኑት ላይ በርሷ ይፈርዳሉ ...»*

አል-ማኢዳህ 5፥46-47 *«በፈለጎቻቸውም (በነቢያቶቻቸው ፈለግ) ላይ የመርየምን ልጅ ዒሳን ከተውራት በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ሲሆን አስከተልን ኢንጂልንም በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት በስተፊቱ ያለችውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ ለጥንቁቆችም መሪና ገሳጭ ሲሆን ሰጠነው የኢንጂልም ባለቤቶች በውስጡ አላህ ባወረደው ሕግ ይፍረዱ አላህም ባወረደው የማይፈርድ ሰው እነዚያ አመጠኞች እነርሱ ናቸው»*

በእነዚህ አንቀጾች በግልጥ ኦሪትና ወንጌል ቀጥተኛ ብርሃን ያለባቸው ስለሆኑ የሚመሩባቸው/አይሁዶችና ክርስቲያኖች/ በነርሱ እንዲፈርዱ ያዛል በነርሱ የማይፈርድ ሰው ግን አመፀኛ ነው በማለት ያስጠነቅቃል::

አል-በቀራህ 2፥136 *«በአላህና ወደኛ በተወረደው (ቁርአን) ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስማኢል ወደ ኢስሐቅም ወደ ያዕቁብም ወደ ነገዶቹም በተወረደው በዚያም ሙሳና ዒሳ በተሰጡት በዚያም ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት ከነርሱ በአንድም መካከል የማንለይ ስንሆን አመንን እኛም ለርሱ (ለአላህ) ታዛዦች ነን በሉ»*

በዚህ አንቀጽ ደግሞ በቁርአን ብቻ ሳይሆን ሙሴና ኢየሱስ ሌሎቹም በተሰጣቸው መጽሐፍ ያለ ምንም ልዩነት ማመን እንዳለባቸው አላህ ሙስሊሞቹን ያዛል ይህም የመጽሐፍቶቹን ተዓማኒነት ለማረጋገጥ ከበቂ በላይ ነው::



www.ethiopianorthodox.org

በተቃራኒ ከሁለቱ መጻሕፍት (ኦሪትና ወንጌል) ጋር የማይስማማ መሆኑ በታወቀ ጊዜ ነበር::

የዚህ አስተሳሰብ ጀማሪ ኢብን ቃሲም የተባለ ሰው ሲሆን ዘመኑ በ1064 ዓ.ም ነበረ:: ይህ ሰው በወቅቱ ከክርስቲያኖች ጋር በሚያደርጋቸው ውይይቶች ቁርአኑ የሚለውና መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው እውነት ልዩነት እንዳለው ተረዳ ቁርአኑ «አልወለደም አልተወለደም» ይላል መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ «አብ ወልድ» ይላል ይህንና ሌሎች መሠረታዊ ልዩነቶች ባየ ጊዜ «ቁርአን ትክክለኛ የሚሆነው እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስህተት ሲሆኑ ብቻ ነው» ብሎ መከራከር ጀመረ ይህ ሰው «ቁርአን ለኦሪትና ለወንጌል ትክክለኛነት ዕውቅና ስለሰጠ እነዚህ የተሳሳቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሆነ ተብሎ ኋላ በክርስቲያኖች የተጨመሩ ናቸው» በማለት ክርክሩን ቀጠለበት በመጨረሻም «በነርሱ ላይ ምስክር እንዲሆንባቸው ለመረጃነት እግዚአብሔር ካስቀራቸው ጥቂት ቃላት በቀር ክርስቲያኖች የመጀመሪያውን ወንጌል አጥተዋል» ሲል አቋም ያዘ:: ቁርአን እውነት እንዲባል መጽሐፍ ቅዱስ ሐሰት (የሰው ቃል የተቀላቀለበት) መሆን አለበት የሚለው የዚህ ሰው የግል ምኞትና ፍላጐት ዓለም አቀፍ ተቀባይነት አግኝቶ እየተቀባበሉ ሲያስተጋቡት እኛ ዘመን ላይ ደርሷል::

ከመሐመድ የቁርአን ምስክርነት በኋላ ቃሉ ተበረዘ የሚለው ይህ አባባል በብዙ የሙስሊም ጸሐፍት እንኳ ተቀባይነት የሌለው ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ ይባስ ብለው በሐዲስ ኪዳን የተገለጠው «የክርስቶስ ልጅነትን» በጳውሎስ የተጨመረ «የሥላሴ ትምህርት» ደግሞ በኒቂያ ጉባኤ ውሳኔ (በ325 ዓ.ም) የተጨመረ ነው በማለት ለወንጌሉ ብቻ



ሳይሆን ለወንጌል የመሰከረውን የራሳቸውን ቁርአን ዕውቅና ያሳጡታል::

ለምሳሌ አንድ የእስላም ጸሐፊ እንዲህ ብለው ነበር -

«የፈጣሪ አንድነት ጥሪ በእስልምና ሃይማኖት ላይ ብቻ የተወሰነ አይደለም:: በቁርአን ውስጥ እንደተጠቀሰ ሁሉ በኦሪትም ሆነ በወንጌል አላህ አንድ የመሆኑ ጉዳይ ተጠቅሷል:: ነገር ግን ክርስቲያኖች ሥላሴን ፈጠሩ:: በመጀመሪያ ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ38 ዓ.ም ጳውሎስ ክርስቲያኖችን ጠርቶ ኢየሱስ የአላህ ልጅ ነው ብሎ ነገራቸው:: አንዳንድ ቡድኖች እሺ ብለው ተቀበሉት:: ከሱ በኋላ ደግሞ ትልቁ ቆስጠንጢን በ325 ዓ.ም በኒቂያ በተደረገው ስብሰባ ክርስቲያኖች በሙሉ ኢየሱስ ፈጣሪ ነው ብለው ማመን እንዳለባቸው ግዴታ ጣለባቸው ከሱ በኋላ ደግሞ ትዮዶስዮስ በ381 ዓ.ም በጠራው የቆስጠንጢኒያ ስብሰባ ላይ የተገኙ ተሰብሳቢዎች መንፈስ ቅዱስን ፈጣሪ እንበለው ብለው ወሰኑ ሆኖም ግን ኢየሱስ ከዚህ ሁሉ የፀዳ ነው::» (አብዱልመሊክ ÷ 7) በጣም የሚያሳዝነው መሐመድ ከተለያዩ የስህተት ሃይማኖቶች ስለ ክርስትና የተዛባ መረጃ ያገኘ እንደነበረ ሁሉ ዛሬም ያሉ ብዙ ሙስሊም ወገኖቻችን ስለ ክርስቲያኖች መረጃ የሚያገኙት የተሳሳተ መረጃ ከሚሰጧቸው የራሳቸው መምህራን ብቻ መሆኑ ነው:: ምክንያቱም አሁን የጠቀስነው መረጃ መጽሐፍ ቅዱሳዊም ሆነ ታሪካዊ ድጋፍ የሌለው ከንቱ ጥላቻ ብቻ የተንጸባረቀበት የሌለ ትምህርት በመሆኑ ነው::

ከእንደዚህ ዓይነቱ ምክንያታዊ አመለካከት ወጣ ባለ መልኩ በታዋቂ የሙስሊም ሊቃውንት የተሰነዘሩትን ምስክርነቶች መመልከቱ ጠቃሚ ነው::



www.ethiopianorthodox.org

*ይከታተላሉ (ትክክለኛ) ትችቱንም አላህ ብቻ እንጂ ሌላ አያውቀውም በዕውቀትም የጠለቁት በርሱ አምነናል ሁሉም ከጌታችን ዘንድ ነው ይላሉ የአእምሮ ባለቤቶችም እንጂ (ሌላው) አይገሠጽም::»*

አላህ በመሐመድ ላይ ያወረደውን መጽሐፍ ሲገልጽ «ግልጽ አንቀጾች» ብቻ ሳይሆኑ እርሱ (አላህ) እንጂ ሌላ የማያውቃቸው አንቀጾችም እንዳሉ ያረጋግጣል:: ግልጽ የሆኑት አንቀጾች እነርሱ የመጽሐፉ መሠረቶች ሲሆኑ ግልጽ ያልሆኑት አንቀጾች ደግሞ ከግልጾቹ ጋር ተመሳሳይ ቢሆኑም ትችት የሚፈልጉ ሰዎች ከነርሱ ተመሳሳይ ሲፈልጉ እንዳያገኙ ግልጽነት የሌላቸው መሆናቸውን ያስረዳል:: ይህ እርስ በርሱ የሚጋጭ አባባል እንደሆነ ግልጽ ነው:: ምክንያቱም የግልጽ ተመሳሳይ ግልጽ ነውና::

በሱረቱ አል-ዙኽሩፍ 43 ፥ 3 «እኛ ታውቁ ዘንድ ዐረብኛ ቁርአን አደረግነው» በማለት ቁርአን ለመካና ለአካባቢው ዐረቦች እንደመውረዱ መጠን ለነርሱ ግልጽ እንዲሆን በዐረብኛ ቋንቋ መውረዱን ተናግሯል:: ግልጽ የሆኑት የመጽሐፉ መሠረቶች የትኞቹ ናቸው? ከመጽሐፉ መሠረት የሚበልጥ ምን ነገር ኖሮ ነው ስውር የሚሆነው? ለሰው ካወረደው በኋላስ ከሰው ለምን ይሰውረዋል? «ግልጽ ያልሆኑ» የተባሉት አንቀጾች ምናልባት ለራሱ ለቁርአን ጸሐፊ ግልጽ ባለመሆናቸው «አላህ ብቻ ያውቃቸዋል» የሚል ሽፋን ተሰጥቶ ቢሆንስ?

*«የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና የሚሠራም ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል:: የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል» (ዕብ 4፥12)*



ከዚህ እውነት የተነሣ የእግዚአብሔር ቃል ባለሥልጣንነት በዘመን ሁሉ የጸና ነው ከሕያው አምላክ የተገኘው ሕያው ቃል በመንፈስ ቅዱስ እንደተገለጠው መረዳቱም በመንፈስ ቅዱስ እገዛ ነው እንጂ ያላመኑ ያመኑም ወገኖች ልዩ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት በቃሉ ውስጥ ስለሚያሻቸው በቃሉ ዙሪያ ያለማቋረጥ ይጸልያሉ ያኔ መንፈስ ቅዱስ በቃሉ ውስጥ ወደ ተገለጸው ከፍ ወዳለው እውነት ሁሉ ይመራቸዋል::

ዮሐ 16፥13 «እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል»

2ቆሮ 3፥6 «ፊደል ይገድላልና መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል»

## 4. <u>ብዙ ገነቶችና ብዙ ሚስቶች</u>

## <u>አንቀጽ 15</u>

*« ከዚኻችሁ የሚበልጥን ልንገራችሁን? በላቸው፡- (እርሱም) ለነዚያ ለተጠነቀቁት ሰዎች በጌታቸው ዘንድ በሥራቸው ወንዞች የሚፈስባቸው ገነቶች በውስጧ ሁልጊዜ ነዋሪዎች ሲሆኑ ንጹሕ የተደረጉ ሚስቶችም ከአላህም የኾነ ውዴታ አላቸው አላህም ባሮቹን ተመልካች ነው»*

ይህ አንቀጽ የሚበልጥ «ታላቅ የምሥራች» ብሎ የሚያሳየው በገነቶች ውስጥ ያሉትን ብዙ ደናግል ሴቶችን ነው በርግጥ ይህ ተስፋ ወንዶቹን እንጂ ሴቶቹን አይመለከትም ሴቶቹንስ ብዙ ወንዶች ይጠብቋቸው ይሆን? ሴት እንኳስ በሰማይ ባል ሊጠብቃት በዚህ ዓለምም ቢሆን ለወንድ መጠቀሚያ እንድትሆን መፈጠሯን በዚህ



www.ethiopianorthodox.org

*እምቢ ቢሉም ባንተ ላይ ያለብህ ማድረስ ብቻ ነው። አላህም ባሮቹን ተመልካች ነው»*

መሐመድና ተከታዮቹ ቁርአኑን ቢጠራጠሩ እንኳ የመጽሐፉን ሰዎች እንዲጠይቁ በዩኑስ 10 ÷ 94 ላይ የታዘዘ ሲሆን በዚህ አንቀጽ የመጽሐፉ ሰዎችን ደግሞ መሐይሞች ይላቸዋል ሰላማችሁን በላቸው ይልና ቢሰልሙ ጥሩ ነው እምቢ ካሉ ግን ያንተ ሥራ መጥራት ብቻ ነው በማለት ሁሉ እስላም እስኪሆኑ ተጋደሉ የሚለውን ትእዛዝ ያፈርሳል እንኳን ያልተቀበሉትን የተቀበሉና ያመኑም ቢሆኑ እውነትን በማስተማር አመንን እስኪሉ ፈቃደኝነታቸውን መጠበቅ እንጂ እሺ ቢሉህ ወይም እምቢ ቢሉህ የሚለው አባባል የተለሳለሰ አስገዳጅነትን ያሳያል እስልምናን ባለመቀበላቸው ምክንያት ብዙዎች ሕይወታቸውን እንዳጡ ልጅ በወላጅ ወላጅም በልጅ መጨከኑን ከእስላም ታሪክ እንረዳለን፡፡ ለምሳሌ በመሐመድ እንደ ጀግና የተተረከላቸው አባቱ እስልምናን አልከተል በማለቱ የገደለው አቡ ኢቤይዳ፣ እናቱን ከሀዲ ነሽ ብሎ ለሞት አሳልፎ የሰጠው የኡማር ልጅ ሞሳብ፣ አባቱ እስልምናን ካልተቀበለ ሊገድለው የዛተው አቡበከርና ሌሎችንም መጥቀስ እንችላለን።

## 7. አላህ የመረዳዳት ወዳጅ ወይስ ጠላት

### አንቀጽ 28

*«ምዕመናን ከሐዲዎችን ከምእመናን ሌላ ረዳቶች አድርገው አይያዙ ይኸንንም የሚሠራ ሰው ከአላህ (ሃይማኖት) በምንም ውስጥ አይደለም ከነርሱ መጠበቅን ብትጠበቁ እንጂ አላህም ነፍሱን (ቁጣውን) ያስጠነቅቃችኋል መመለሻም ወደ አላህ ብቻ ነው»*



ይህ አንቀጽ ፍቅርን የሚገልጥ ባይሆንም የሙስሊሙን ዓለም ኅብረትና አንድነት ለመጠበቅ የገባ መልእክት እንደሆነ እንረዳለን አላህ የፍጥረት ሁሉ ረዳት ከሆነ በርሱ ያመኑ ሙስሊሞች ያላመኑ ሰዎችን ረዳት ወዳጅ አድርገው እንዳይዙ ማዘዙ ለምን? በዚህም ቃል እንኳ ብንስማማ ታላላቅ ሙስሊም የዐረብ መንግሥታት ከምዕራባውያን (ክርቲያን መንግሥታት) ጋር ባላቸው ኅብረትና ከነርሱ በሚያገኙት እገዛ የተወገዙ መሆናቸው ነው። ቃሉ የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን ጨርሶ እንደ ሙስሊም የማይመለከት ሊሆን ይችላል ምክንያቱም እስልምና በእንግድነት በ615 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በክርስትናው የመረዳዳትና የመተጋገዝ መንፈሳዊ ባህል የተቀረጹት ሙስሊሞች ከዚህ አንቀጽ ጋር የማይሄዱ በመሆናቸው ምናልባት እንደ ከሃዲ ሊቆጠሩ ይችሉ ይሆናል ከመንፈሳዊው ብቻ ሳይሆን ከማኅበራዊው ሕይወት አንፃር ይህ አንቀጽ ሚዛን የማይደፋ ሲሆን ሌላ ጥያቄ እንድናነሳም ያደርገናል ሙስሊሙ ከሙስሊም ውጪ ረዳት አድርጐ አይያዝ ከተባለ ሙስሊሙስ የተቸገረና የተጐዳን ከእስልምና ውጭ ያለ ሰው ቢረዳ አላህ ያዝን ይሆን? እርሱስ እንደ ከሃዲ ይቆጠር ይሆን? አንድ ምጽዋት የሚሰጥ ሙስሊም ሃይማኖት እየጠየቀ ነው ወይስ እጁን ለዘረጋለት ድሃ ሁሉ?

*«ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው»* (ማቴ 7 ÷ 12)



www.ethiopianorthodox.org

## 8. በሥራ፣ በአላህ ምሕረት ወይስ በአላህ ቅድመ ውሳኔ?

## የሚጣረሰው አንቀጽ 30

*«ነፍስ ሁሉ ከመልካም ነገር የሠራችውን የቀረበ ሆኖ የምታገኝበትን ቀን (አስታውስ) ከመጥፎም የሠራችው በርስዋና በርሱ (በኃጢአትዋ) መካከል በጣም የሰፋ ርቀት ቢኖር ትመኛለች አላህ ነፍሱን ያስጠነቅቃችኋል አላህም ለባሮቹ ርኅሩህ ነው»*

ይህ ቃል በግልጥ የሚያሳየው ሰው ሁሉ እንደ ሥራው መጠን እንደሚከፈለው (እንደሚፈርድለት ወይም እንደሚፈረድበት) ሲሆን እያንዳንዱ በሥጋው በዘራው መጠን በነፍሱ ያጭዳል ማለት ነው (7 ÷ 8 -9) አንቀጹ በግልጥ አላህ ለባሮቹ ርኅሩህ ቢሆንም እንኳ ትክክለኛ ፈራጅ በመሆኑ ማንም የሚድነው በሠራው በጎ ሥራ መሆኑን ያረጋግጣል:: እስልምና ድህነት (ዘላለማዊ ሕይወት) የሚገኘው በሥራ ነው ብሎ የሚያምን እምነት ሲሆን የእስልምና የእምነት መሠረቶች 5 ናቸው እነርሱም-

1. የእምነት ምስክርነት (አላህ አንድ ነው መሐመድ የአላህ ነቢይ ነው) (ሸሃድ)
2. ሶላት መስገድ
3. ዘካ (ምጽዋት) መስጠት
4. ረመዳን መጾም
5. ሐጂ ማድረግ (የቻለ መካ ሄዶ መስገድ) ናቸው::

የእነዚህን ምግባራት መንፈሳዊ ይዘት አሁን በዝርዝር መፈተሽና ማየት ባያስፈልገንም አንድ ሙስሊም በፈጣሪው ማመኑንና ለርሱም ታዛዥነቱን የሚያሳይባቸው መንገዶች ተደርገው ይወሰዳሉ



መንፈሳዊው ዓለም ሰው ከፈጣሪው ጋር ብቻ በሚያደርገው ኅብረት የሚወሰን ሳይሆን ሰዎች ከሰዎች ጋር የሚኖራቸውን የግንኙነት አቅጣጫ የሚወስን በመሆኑ ስርቆትን ግድያን ዝሙትን የሚያከለክል ባልንጀራን (ማንኛውንም ሰው) እንደ ራስ አድርጎ መውደድን የባልንጀራን ሚስቱን ንብረቱን አለመመኘትን የማያዝ ሃይማኖት የለም::

አንድ ሙስሊም ከዳነ የሚድነው ከማያየው አላህ ጋር ያለውን ግንኙነት በማሳመር ብቻ ሳይሆን ከሚያየው ወንድሙም ጋር ያለውን ግንኙነት በሕጉ በተጻፈው መሠረት በፍጽምና መከወን ከቻለ ብቻ መሆኑን ነው መነሻ ያደረግነው አንቀጻችን የሚያረጋግጠው:: ነገር ግን የትኛውንም ሙስሊም ገነት እንደምትገባ ርግጠኛ ነህን? ብላችሁ ጠይቁት ይህን ከአላህ በቀር የሚያውቅ የለምና ርግጠኛ አይደለሁም ይላችኋል ይህ የሚያሳየው ይህ ሰው (ሙስሊም) በርግጠኝነት እንከን ሳይገኝበት መቶ በመቶ የአላህን ፈቃድ ፈጽሞ (ሕጉን ያለ ማጓደል ጠብቆ) የፍርዱን ሚዛን ሞልቶ ከቁጣው መዳን እንደማይችል ርግጠኛ ስለሚሆን ነው ታዲያ እንዴት ልትድን ትችላለህ? ብላችሁ ብትጠይቁት ግራ ሊገባው ይችላል እርሱ ባይመልስም እንኳ ቁርአን ሌላ መልስ አለው ከመነሻ አንቀጻችን ቀጥሎ ያለው አንቀጽ ደግሞ ሌላ (ተቃራኒ) የድህነት መንገድ ያሳየናል አሊ-ኢምራን 3 ÷ 31 እንዲህ ይላል::

> *«በላቸው:- አላህን የምትወዱ እንደሆናችሁ ተከተሉኝ አላህ ይወዳችኋልና ኃጢአቶቻችሁንም ለናንተ ይምራልና አላህም መሐሪ አዛኝ ነው»*



www.ethiopianorthodox.org

አላህን የሚወዱ ፈቃዱን እንዲያደርጉ ሳይሆን መሐመድን እንዲከተሉ ይጋብዛቸዋል አላህም መሐመድን ስለተከሉ ብቻ ይወዳቸዋል ከዚህም የተነሳ ኃጢአቶቻቸውን ይምራቸዋል እዚህ ላይ የተጠቀሰ አንዳች በጐ ሥራ የለም የመሐመድ ተከታይ (ሙስሊም) ብቻ በመሆን አላህ ኃጢአትን ይተዋል ይቅር ይላል ከዚህ አንቀጽ የምንረዳው ቅድም ሕግን ጠብቆ ለመዳን ሲታገል የነበረውና እንደማይቻል የተረዳው ሙስሊም በአላህ ምሕረት ሊድን እንደሚችል ይገምታል:: ይህ ሙስሊም መዳን ስለመቻሉ እርግጠኛ አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን አንዴ ወደ መልካም ሥራው ሌላ ጊዜ ደግሞ ወደ አምላክ ምሕረት የሚያንጋጥጥ ያላረፈ ነፍስ ያለው በመሆኑ ያሳዝናል ውስጡ ያላረፈበት ምክንያት በመልካም ሥራ ከሆነ በፍጹሙ መለኮታዊ ዳኝነት ፍርድ ውስጥ ማለፍ እንጂ ምሕረት መጠበቅ እንደማይገባ በምሕረቱ ላይ ከተደገፉ ደግሞ የራስን ደካማ ሥራ ማሰብ እንደማይገባ ህሊናው ስለሚመሰክርለት ነው ከርሱ ጐደሎ ሥራ ይልቅ ፍጹሙ የአምላክ ምሕረት አስተማማኝ ቢሆንም ይህን መቀበል መቻሉን የሚያረጋግጥበት ዋስትና የለውም ከዚህ የተነሳ የሕይወት ያውም የዘላለም ሕይወት በሆነው ጉዳይ ውስጥ እርስ በርሳቸው በሚጣረሱ አደገኛ አስተሳሰቦች መሃል ይሰቃያል::

ይህ ችግር ሳይፈታ ደግሞ ሌላ ሦስተኛ ተቃራኒ መንገድ ቁርአን ያሳየናል በሁድ 11 ÷ 119 ላይ

*«ጌታህ ያዘነለት ብቻ ሲቀር (ከመለያየት አይወገዱም) ለዚሁም ፈጠራቸው የጌታህም ቃል ገሀነምን ከአጋንንትና ከሰዎች ከሁሉም በርግጥ እሞላታለሁ በማለት ተፈጸመች»*



«ሕጉን በመጠበቅና መልካም ሥራን በመሥራት ወይስ በአምላክ ምሕረት» የሚሉትን ሁለት የተለያዩ የመዳን መንገዶች የሚቃረነው ይህ አንቀጽ ደግሞ አላህ አዝኖ ገነት ከሚያስገባቸው ውጭ ያሉት ሰዎች ገሃነምን ለመሙላት መፈጠራቸውን ያሳየናል ከሰዎች ብቻ ሳይሆን ከአጋንንትም ጭምር ገሃነምን ለመሙላት ሲል ብቻ የፈጠራቸው እንዳሉ እንረዳለን አላህ ከፍጥረቱ መዳን ይልቅ የገሃነም አለመሙላት ለምን ያስጨንቀዋል? አሁን በጐ ምግባር ወይም የአምላክ ምሕረት ለውጥ አያመጡም ገሃነምን ለመሙላት ከሆነ የተፈጠርነው ወደዛ መንገዝና ሄዶ መሙላት ነው ይህን የሚያውቀውና የወሰነው አላህ አስቀድሞ በመሆኑ የርሱ ምሕረትም ሆነ ያንተ ልፋት ትርጉም የላቸውም ምክንያቱም አንቀጹ በግልጥ «ለዚሁም ፈጠራቸው» በማለት ደምድሞታል:: ከሚታዘዝላቸው ሰዎች ውጭ ያሉት ሰዎች ገሃነምን መሙያ እንደሆኑ ሁሉ ጥቂት ከገሃነም የሚያመልጡ የሚታዘዝላቸው አጋንንትም ከገሃነም ያመልጣሉ እንግዲህ ገነት ሰዎችና አጋንንት ተባብረው የሚኖሩባት አገር መሆኗ ነው አጋንንት (ሰይጣናት) እጅግ ክፉዎች የመልካም ነገር ሁሉ ጠላት ሲሆኑ አላህ ግን ካዘነ የትኛውንም ክፉ ሥራቸውን ቸል ብሎ ለገነት ያበቃቸዋል በምድር ጠላቶች የነበሩት ሰውና አጋንንት በገነት ወዳጆች ሆነው ይኖራሉ:: አንባቢ ሆይ አይከብድም? ታዲያ መልካም ሥራ? የአምላክ ምሕረት? ወይስ የአላህ ውሳኔ?

*«ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም»* (ዮሐ 1÷12-13)



www.ethiopianorthodox.org

ልናገኝ እንችላለን:: መሐመድ ተናግሮት የተፈጸመ ትንቢት ወይም ያደረጋቸው ተአምራት በቁርአን ውስጥ እንኳ አለመጠቀሳቸው ሌላ ጥያቄ ያስነሳል:: ባነሳነው አንቀጽ ላይም ይህ ችግር ይስተዋላል መታዘዝ ፈጣሪን ወይስ ፍጡርን? መሐመድ ሃይማኖት ሁሉ ለአላህ ብቻ (እስልምና ብቻ እስኪኖር) እስኪሆን እንዲዋጉ ካዘዘ በኋላ ሌላ ቦታ ደግሞ መዋጋት ሳይሆን የርሱ ድርሻ ቃሉን ማድረስ እንደሆነ ተጽፏል:: በሁለተኛው መንገድ እንስማማና የሰዎች መታዘዝ ወይም አለመታዘዝ ለመሐመድ ወይስ ለቃሉ ባለቤት ለአላህ? የመሐመድን ሰይፍ ፈርተው ታዘዝን ያሉ ብዙ ሰዎች ይኖራሉ ታዲያ እነዚህ ለአላህ ታዘዙ ማለት ነው? ከምንሞት ብለው «አላህ አንድ ነው መሐመድ የአላህ መልክተኛ ነው» ብለው ያወጁ ሰዎች ለአላህ ታዘዙ ማለት ነው? መሐመድ ራሱ የአላህ ታዛዥ ከሆነ ለኔና ለአላህ ታዘዙ ማለትስ አለበት?

«ብትሸሹ አላህ ከሐዲዎችን አይወድም በላቸው» የሚለውም ቃል የእውነተኛውን አምላክ ባሕርይ አያሳይም ምክንያቱም የሚለዋወጥ ፍቅር ከሁኔታዎች ጋር የተያያዘ ፍቅር ግብዝነት ያለበት ፍቅር ሲሆን አላህ ሲታዘዙት የሚወድ እምቢ ሲሉት የሚጠላ ከሆነ መለኮታዊው አምላክ አለመሆኑን ያረጋግጣል:: ይህ የሰው ባሕርይ ነው እግዚአብሔር ፍቅር ነው ማንንም መጥላት አይችልም:: ስለዚህ ከሐዲ የተባሉትን ሰዎች ሳይሆን ክህደትን ይጠላል አምላክ ሰዎችን በኃጢአታቸው ሲቀጣ እንኳ እውነተኛ ፈራጅ ስለሆነ እንጂ ጠልቷቸው አይደለም የማይታዘዙትን ሰዎች መሐመድ ይጠላ ይሆናል ነገር ግን አላህም አብሮ ከጠላ ታዲያ አላህ ማን ነው?



«ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና:: ስለ ጻድቅ የሚሞት በጭንቅ ይገኛልና ስለ ቸር ሰው ግን ሊሞት እንኳ የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል:: ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል ይልቁንስ እንግዲህ አሁን በደሙ ከጸደቅን በእርሱ ከቁጣው እንድናለን:: ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን::» (ሮሜ 5 ÷ 6 - 10)

## 10. ኢምራን ማን ነው?

## አንቀጽ 33

«አላህ አደምን ኑሕንም የኢብራሂምንም ቤተሰብ የዒምራንንም ቤተሰብ በዓለማት ላይ መረጠ»

ብሉይና ሐዲስ ከሚለው የሁለቱ ታላላቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስያሜ ጀምሮ በመጽሐፍ ቅዱስ የተካተቱት መጻሕፍት በጸሐፊው ወይም በመጽሐፉ ጠቅላላ ይዘት የተሰየሙ ናቸው ለምሳሌ ዘፍጥረት ከፍጥረት ጀምሮ የሰው ልጅን የቀደመ ታሪክ የሚናገር፤ ዘጸአት (ጸአት - መውጣት) ስለ እስራኤል ልጆች ከግብጽ ባርነት መውጣት፤ መጽሐፈ ሳሙኤል (በሳሙኤል የተጻፉ) መ. አስቴር (እግዚአብሔር በአስቴር ለእስራኤል የገለጠውን ማዳን የሚናገር) ወዘተ በማለት ተሰይመዋል:: ቁርአን በአንድ ሰው በመሐመድ በኩል የተገለጠ አንድ መጽሐፍ ነው:: በውስጡ 114 ምዕራፎች ሲኖሩ እንኳን በ114ቱ ምዕራፎች መካከል ቀርቶ በአንዱም ምዕራፍ ውስጥ



www.ethiopianorthodox.org

ዘካርያስ በማርጀቱ ሚስቱ ኤልሳቤጥ ደግሞ መካን በመሆኗ ምክንያት ልጅ ስላልወለዱ ዘካርያስ ያቀርበው የነበረው ጸሎት በቁርአን ተጽፏል (3÷38) እንደ ቁርአኑ አገላለጽ የማርያም አባት እና እናት የእርጅናም ሆነ የመካንነት ችግር ያለባቸው አይመስልም አስቀድመን ባየነው አንቀጽ ላይ «የዒምራን ቤተሰብ» የሚለው ሀረግ የቤተሰቡን (የመውለድ ችግር እንዳሌለባቸው) ለማሳየት የገባ ይመስላል:: ዘካርያስ ልጅ ስለሌለው ልጅ እንዲሰጠው ከጸለየ ሃና እና ኢምራን ስለ ልጅ ስእለት የሚሳሉት በመውለዳቸው ወይስ ባለመውለዳቸው? የሚወልዱ ከሆነ ስእለት መግባት ለምን ያስፈልጋል? የወለዱትን ወስዶ መስጠት እንጂ!! የማይወልዱ ከሆነ ደግሞ ልጅ ብትሰጠን ላንተ እንሰጥሃለን ብለው ሊሳሉ ይችላሉ:: ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የምናስተውለው እውነታ ነው ልጅ ላልነበራቸው ለማኑሄና ለሚስቱ ስለ ሶምሶን መወለድ ያበሰረው መልአክ ልጁ ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ለእግዚአብሔር የተለየ እንደሚሆን ነግሯቸዋል (መሳ. 13÷2- 5) እንዲሁም የሕልቃና ሚስት ሃና ልጅ እንዲሰጣት ስትለምን «ዕድሜውን ሁሉ ለእግዚአብሔር እሰጠዋለሁ ...» ብላ መሳሏን እንመለከታለን (1ሳሙ. 1 ÷ 11) አብርሃምና ሣራ ይስሐቅና ርብቃ ያዕቆብና ራሔል ልጅ ባለመውለዳቸው ምክንያት በእግዚአብሔር ፊት ያዝኑ እንደነበር እናያለን የሁሉንም ጸሎት የሰማ አምላክ ባለ ልጅ አድርጓቸዋል:: (ዘፍ 15 ÷ 1 - 5፤ 25 ÷ 21፤ 30 ÷ 1 - 2፤ 22)

ወደ ቁርአኑ አገላለጽ ስንመለስ ግን ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ልምምድ የወጣ ነገር ያሳየናል:: ሃና በሆዷ ያለውን ፅንስ እንደ ወንድ እያሰበች ለእግዚአብሔር ትሳላለች ምናልባት ይህ ልዩነት ሊፈጠር



የቻለው ቁርአኑ አብዛኛውን ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ ስለሚከተል ሊሆን ይችላል ምክንያቱም የዘካርያስና ኤልሳቤጥ እርጅናና መካንነት በመጽሐፍ ቅዱስ የተዘገበ ሲሆን ቁርአኑ ደግሞታል በድንግል ማርያም ወላጆች ላይ የነበረው ተመሳሳይ ችግር በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተዘገበ ባለመሆኑ ቁርአኑ የዘለለው ሲሆን የተሳሳተ መረጃ እንዲሰጥ ተገድዷል::

ድንግል ማርያም መካን ከሆኑና ብዙ ዘመን በቅድስናና በትጋት (በልመና) ከኖሩ ቅዱሳን እንደ ይስሐቅ በሽምግልና ዘመናቸው የወለዷት መሆኗ ቀርቶ በሥጋ ፈቃዳቸው ከወለዷቸው ልጆቻቸው አንዷ ሆና መቆጠሯ፤ ጉልበታቸው ከዛለ በኋላ (መውለድ የማይችሉ ከሆኑ በኋላ) የጸና ልመናቸውን ለመፈጸም ብቻ ሳይሆን የዘላለም አሳቡን ለመፈጸም ከርሱ በሆነ ኃይል (ተአምራት) የተወለደች ሳትሆን እንደ ሌሎቹ ልጆቻቸው ተጸንሳ ሳለ ወንድ ከሆነች ላንተ እንሰጣለን ብለው ተስለው የወለዷት ሆና መቆጠሯ ለርሳ ከዚያም ከርሷ ለሚወለደው የሚሰጠውን ክብር እንደሚቀንስ ከታሰበ የዋህነት ነው:: ምክንያቱም እግዚአብሔር እንደ ሰው አስቦ ሠርቶ አያውቅምና:: እንደ አጋጣሚ የተጸነሰችና ከተጸነሰችም በኋላ ወንድ ከሆነች በሚል ለእግዚአብሔር የተሳለች ልጅ እንደ ሆነች ከታሰበ አንቀጽ 42 ላይ «በዓለማት ሴቶች ላይ መረጠሽ» የመባሏ ምክንያት ትርጉም አልባ ይሆናል:: ለመሆኑ ሴት ልጅ ለእግዚአብሔር ሥራ አታስፈልግምን? ቅዱሳኑ ያታ ለይተው ነው የሚለምኑት? ወይስ ይህ የቁርአን አስተሳሰብ?



www.ethiopianorthodox.org

## 12. ማርያምን ማን አሳደጋት?

### የሚጣረሰው አንቀጽ 37

*«ጌታዋም በደህና አቀባበል ተቀበላት በመልካም አስተዳደግም አፋፋት ዘካሪያም (ዘካሪያስ) አሳደጋት ዘካሪያ በርሷ ላይ በምኩራቧ (በመጸለያ ስፍራዋ) በገባ ቁጥር እርስዋ ዘንድ ሲሳይን አገኘ መርየም ሆይ ይህ ላንቺ ከየት ነው? አላት፦ እርሱ ከአላህ ዘንድ ነው አላህ ለሚሻው ሰው ሲሳዩን ያለ ድካም ይሰጣል አለችው»*

ምክንያቱን ባይገልጽም የድንግል ማርምን ልዩ አስተዳደግ የሚገልጸው ይህ አንቀጽ ስለ አሳዳጊዎቿ የሚሰጠው መረጃ እርስ በርሱ ይጋጫል:: ማርያም የስእለት ልጅ መሆኗ በቤተ መቅደስ ማደጓ የሰማይ ሕብስት እየተመገበች ማደጓን ይገልጻል እነዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፉ ባለመሆናቸው መሐመድ ከአዋልድ መጻሕፍት ያገኛቸው ናቸው:: «ጌታዋ በመልካም አስተዳደግ አፋፋት» ብሎ በቤተ መቅደስ በጌታ ልዩ እንክብካቤ (መለኮታዊ ጥበቃ) ማደጓን ከነገረን በኋላ ወዲያው ቀጥሎ «ዘከሪያም አሳደጋት» ይለናል:: አሳዳጊው ታዲያ ማን ነው? ጌታ ወይስ ዘካሪያስ? እነዚህን ሁለት አሳዳጊዎች ቦታ የሚያሳጣ ሌላ አሳዳጊ ደግሞ አንቀጽ 44 ላይ እናያለን -

*«ይህ ወዳንተ የምናወርደው የሆነ ከሩቅ ወሬዎች ነው:: መርየምን ማን እንደሚያሳድግ ብርዖቻቸውን (ለዕጣ) በጣሉ ጊዜ እነሱ ዘንድ አልነበርክም በሚከራከሩም ጊዜ እነሱ ዘንድ አልነበርክም»*

በርግጥ ቁርአኑ ይህን አንቀጽ «የሩቅ ወሬ ነው» በማለት ጠርቶታል ከሰማይ ወረደ የተባለው ቃል የሩቅ ወሬ ተብሎ መቅረቡ ግራ



የሚያጋባ ሲሆን በርግጥም የተዛባ መልዕክት የያዘ አንቀጽ ነው የስእለት ልጅ የሆነችው ድንግል ማርያም ወደ ቤተ መቅደስ ገብታ ሰማያዊ ሕብስት እየወረደላት አላህና ዘካርያስ እያሳደጓት ሳሉ ሌሎች መጥተው እሷን ለማሳደግ ዕጣ የሚጣጣሉበት ምክንያት ምንድነው? የስእለት ልጅ በመሆኗ ለእግዚአብሔር ከተሰጠችና ቤተ መቅደስ ከገባች በኋላ አምላክም ተቀበሏት ምግቧን ከሰማይ እያወረደ በመመገብ በጸጋና በቅድስና ካሳደጋት ሌላ የተሻለ አሳዳጊ ከየት ሊመጣ ነው? ለምን? ሌሎች ከሚያሳድጓትስ ወላጆቿ አያሳድጓትምን? አንድ ነገር ምንጩና ጊዜው እየራቀ ስለሚሄድ ከእውነት እየራቀ መሄዱ አይቀርም ይህም ከሩቅ የሆነ ወሬ መባሉ አግባብ ነው:: ዕጣው ለማን እንደወጣና ሦስተኛ ደግሞ ማርያምን ማን እንዳሳደጋት ብናውቅ ጥሩ ነበር አልተገለጸም እንጂ:: ቁርአን የተለያዩ ምንጮች ያሉት መጽሐፍ መሆኑ ለብዙዎቹ ግጭቶች ዋነኛ መንስኤ እንደሆነ አያጠራጥርም::

እመቤታችን 3 ዓመት በወላጆቿ ቤት 12 ዓመት በቤተ መቅደስ ካደገች በኋላ ንፅህናዋን ያልተረዱ አይሁድ ለአቅመ ሄዋን ደርሳለችና ከመቅደሳችን ትውጣ ብለው ባጉረመረሙ ጊዜ ዘካሪያስ ሚስቶቻቸው የሞቱባቸው አረጋውያንን ጠርቶ በትሮቻቸውን ሰብስቦ ጸለየበት ከዳዊት ዘር የሆነው ዮሴፍ በትሩ ለምልማ አፍርታ አገኛት ጠብቃት ብሎ ሰጠው ዮሴፍም ጠባቂዋ (እጮኛዋ) ተባለ እንግዲህ የ15 ዓመቷን ድንግል ማርያምን ለመጠበቅ እንጂ ህፃኗን ማርያም ለማሳደግ አልነበረም ዕጣ የተጣለው የሩቁ ወሬ ግን ዕሩቅ ነው::



www.ethiopianorthodox.org

በማታና በጣትም አወድሰው» ይለዋል:: እንደበቱ የተዘጋ ሰው እንዴት አድርጎ ይሆን ጠዋትና ማታ የሚያወድሰው?

## 15. ምክንያት አልባው የማርያም በዓለማት ሴቶች ላይ መመረጥ

### አንቀጽ 42

*«መላእክትም ያሉትን (አስታውስ)፡- መርየም ሆይ! አላህ በእርግጥ መረጠሽ አነጻሽም በዓለማት ሴቶችም ላይ መረጠሽ»*

በቁርአን ውስጥ የተጠቀሰ ብቸኛ የሴት ስም የማርያም ስም መሆኑንና ምክንያቱን ቴቄል ክ. 1 ገጽ 23 ላይ አይተናል:: በዚህ አንቀጽ ላይ ደግሞ ሌላ ለየት ያለ ነገር ግን ቁርአን ምክንያታዊ የማይሆንበትን አሳብ እናገኛለን:: ይህውም-

- የማርያም መመረጥ
- መንጻት
- በዓለማት ሴቶች ላይ መመረጥ ናቸው::

አላህ ማርያምን ለምን መረጠ? ያውም በዓለማት ሴቶች ላይ! ከምንስ ነው ያነጻት? እንዴት ነው ያነጻት? ለምንድነው ያነጻት? ቁርአን እነዚህን ጥያቄዎች አለመመለሱ ብቻ ሳይሆን የሚመልስበትም ምክንያት የለውም:: ነገር ግን አሳቡ በመጠኑ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰደ ቢመስልም ያለውን ትልቅ ልዩነት እናያለን::

አስቀድመን ባየናቸው አንቀጾች ላይ እንደተገለጸው የዮሐንስን ታሪክ ሳይጨርስ ቁርአኑ ወደማርያም ብስራት ይገባል:: በመጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ገብርኤል ለዘካርያስ ባበሰረ በስድስተኛው ወር ወደ



ናዝሬት እንደሄደና ለማርያም እንዳበሰራት ሁሉ ቁርአኑም ጊዜውንና ቦታውን የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ ባይሰጥም የታሪኩን ቅደም ተከተል ግን ይከተላል:: ቅዱስ ገብርኤልም ያልተለመደ አዲስ ሰላምታ ያቀርብላታል-

*«ደስ ይበልሽ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ ጌታ ካንቺ ጋር ነው አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አሏት»*

በኃጢአት ምክንያት እግዚአብሔር ስለተለየው ከጸጋ በተራቆተው ዓለም ውስጥ ይህ ምስጋና አዲስ ምስጋና ነበር ጌታ ከርሷ ጋር ያልነበረበት ጊዜ ስላልነበረ አንዳች ጸጋ ያልጐደላት በመሆኗ ከሴቶች ሁሉ ልዩ ናት ቃሉ ጸጋ ይሞላብሻል ከሴቶች መካከል ትባረኪያለሽ እንዳላለ ግልጽ ነው ስለዚህ ይህ ምርጫ በጊዜ ያልተወሰነ ዘላለማዊ ምርጫ ነው ማለትም የዘላለማዊው አምላክ መለኮታዊ ዕቅድ ነው:: ይህ ምርጫ ልዩ ስለሆነ ደስ ይበልሽ ይላታል:: ይህ የዓለም ሁሉ ደስታ ነው:: ሁለቱን ምርጫ ስናነጻጽር-

ቁርአኑ - በዓለማት ሴቶች ላይ መረጠሽ - በዓለም ካሉ ሴቶች አንዷ ስትሆን በነርሱ ላይ ተመረጠች

መ/ቅዱስ - ከሴቶችመካከል የተባረክሽ ነሽ - ከሴቶች ሁሉ መሃል እንደርሷ በጸጋ ምልአት የከበረ ስለሌለ ተባረከች (ተመረጠች)

በዓለም ላይ ባሉ ሴቶች ላይ መመረጥ እና ከሴቶች ሁሉ ልዩ ሆኖ መመረጥ ትልቅ ልዩነት አለው ይህ ልዩነት የበለጠ ጐልቶ የሚታየው የምርጫው ምክንያት ሲረዳ ነው ቁርአን ማርያምን በዓለማት ሴቶች ላይ መረጠሽ ሲል የዚህን ምርጫ አስፈላጊነት በምክንያት አያስረዳም የማርያምን መመረጥና መንፃት ከሚናገረው አንቀጽ ቀጥሎ ያለው አንቀጽ «ታዘዢ፣ስገጂ፣ ከአጐንባሾች ጋር አጐንብሺ» የሚል መመሪያ



www.ethiopianorthodox.org

ለማርያም ያስተላልፋል ስለዚህ ቁርአን የማርያምን በዓለማት ሴቶች ላይ መመረጥና መንጻት» ምክንያት ዘሎታል ማለት ነው መቼም እንደየትኛውም ሰው ለማጉንበስ ለመስገድና ለመታዘዝ ልዩ የሆነ መመረጥና መንጻት እንደማያስፈልግ መልአክም ይህን ብስራት ይዞ ከሰማይ መውረዱ እንደማያስፈልግ ግልጽ ነው ይህን ልዩ የመመረጥ ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስ በሚገባ ያብራራዋል:: በከንቱ ውዳሴ ለመጣል የመጣ ፈተና እንዳይሆን ለመመርመር ድንግል ማርያም የበዛውን ምስጋና ቶሎ አልተቀበለችም ይልቁንም ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው ብላ አሰበች::

መልአኩም መልሶ የከበረውን ሰላምታ ምክንያት

*«ማርያም ሆይ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋን አግኝተሻልና አትፍሪ እነሆም ትጸንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዛለም ይነግሣል ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም»* በማለት አስረድቷታል::

እንዴት ግሩምና ግልጽ ቃል ነው:: ይህም የብዙ ነቢያት ትንቢትና ለብዙ አባቶች በምሳሌ የተገለጸ ታላቅ እውነት ነው (ኢሳ 7፥14፤ 9፥6 ፤ዳን 4፥ 44፤ ሚክ 5፥ 2 ... ) በዚህ ቃል ውስጥ በግልጽ እንደተቀመጠው የማርያም ልዩ የሆነ ምርጫ

- ታላቅ የሆነው ጌታ
- የእግዚአብሔር ልጅ
- ዘላለማዊ ሥልጣንና መንግሥት ያለው ጌታ ከርሷ ስለሚወለድ መሆኑን አስረድቷታል:: ስለዚህ ልዩ የሆነው ምርጫ ልዩ ስሆነው ጌታ ነው ማለት ነው:: ይህ በርግጥ ምክንያታዊ ነው::



በመቀጠል ሁለተኛውን ቃል (የቁርአኑን) ስንመለከት «አነፃሽ» ይላል ከምንድነው ያነፃት? ከኃጢአት የሚል መልስ የሚሰጥ ከሆነ «አላህ በደህና አቀባበል ተቀበላት በመልካም አስተዳደግም አፋፋት» የተባለችው መርየም ኃጢአት ነበረባት? አሁንም ኃጢአት አለባት የሚባል ከሆነ ምን ዓይነት ኃጢአት?» በጣም እውነተኛ ናት» (አል-ማኢዳህ 5፥ 75) የሚለው ቃልስ? በጣም እውነተኛ ከሆነች ከሐሰት (ከኃጢአት) ጋር ኅብረት የላትምና:: አሁንም እንኳ ኃጢአተኛ ናት የሚባል ከሆነ እላይ ከነሳናቸው ቃላት ጋር የሚጋጭ ቢሆንም መቼና እንዴት (በምን ዓይነት አሠራር) አነፃት? እርሷን ፍጹም ንጹሕ ማድረግስ ለምን አስፈለገ? ከርሱ በፊት ካለፉት ነቢያት እንደ አንዱ የሆነውን ኢሳን ስለምትወልድ ወይስ ንጹሑን ጌታ ስለምትወልድ? ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ከመጣን ግን ለዚህ ችግር ግልጽና ምክንያታዊ መረጃ እናገኛለን:-

አስቀድመን የመልአኩን ሰላምታና የማርያምን ጥያቄ የሰላምታው ምክንያትና የመመረጧ ዓላማ የጌታ መወለድ መሆኑን አይተናል አሁን ማርያም አስደናቂውንና የሚጠበቀውን ብስራት ተቀብላ እርሷ ንጽሕት በመሆኗ «ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል» በማለት የልደቱን ምሥጢር ትጠይቃለች መልአኩም-

> « *መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግም ካንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል ...»* በማለት ታላቁን የሥላሴ ምሥጢር ያስረዳታል::



www.ethiopianorthodox.org

መመለስ ስለነበር በሞቱ ተስፋ የቆረጡ ሲሆን ከተነሳም በኋላ ከማረጉ በፊት ይህን ጥያቄ አቅርበዋል።

«እኛ ግን እስራኤልን እንዲቤዠ ያለው እርሱ እንደሆነ ተስፋ አድርገን ነበር» (ሉቃ 24፥ 21)

«እነርሱም በተሰበሰቡ ጊዜ፦ ጌታ ሆይ በዚህ ወራት ለእስራኤል መንግሥትን ትመልሳለህን? ብለው ጠየቁት...» (ሐዋ ሥ 1፥ 6) እንግዲህ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መባሉ በሉቃስ 19 ፥ 10

«የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአልና» ብሎ እንዳስተማረን በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር በመለየቱ የሞትና የሰይጣን ባሪያ የሆነውን የሰውን ልጅ ለማዳን ነው። በመንፈስ ቅዱስ መውረድ የክርስቶስ ምድራዊ ተልዕኮ የገባው ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጴጥሮስም-

*«እግዚአብሔር የናዝሬቱ ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀባው እርሱም መልካም እያደረገ ለዲያብሎስም የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ»* (ሐዋ. ሥ 10 38) በማለት የመሢሕነቱን (የመቀባቱ) ሥራ የሰይጣንን ሥራ ማፈራረስና የሰውን ልጅ ወደዘላለም ሕይወት (መንግሥት) ማምጣት እንደነበር አስረዳን።

*«የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ»*

(1ዮሐ 3 ፡ 8)

ስለ ክርስቶስ መሲሕነት ይህን ያህል መናገር ያስፈለገን ቁርአን ኢየሱስን «መሢሑ» ሲለው ይህን የሚሢሕነቱን ሥራ አምኖ ወይስ ሳያምን? ካላመነ ታዲያ «አል-መሢሕ ኢሳ» ምን ማለት ነው? የተቀባ ነገር ግን ነፃ የማያወጣ መሢህ አለን? በቁርአን ውስጥ ከኢየሱስ በቀር በዚህ ቅጽል የተጠራ ነቢይ አለን? ኢየሱስ



ማለት መድኃኒት (አዳኝ) ማለት መሆኑንስ ቁርአን ይቀበላል? ካልተቀበለ ግን ሥራውን (ሕይወቱን) የማይተረጉም (የማያረጋግጥ) ስም እርሱ ይይዛልን? መሢሕ ኢየሱስ የሚለውን ስም ልክ እንደ እኛ ሙስሊም ወገኖቻችን ከተቀበሉ ቅቡዕነቱን - ነፃ አውጪነቱንና አዳኝነቱን እንዲቀበሉ በእግዚአብሔር ፍቅር እንጋብዛቸዋለን። አይሁድ በተሳሳተ መንገድ የሚጠብቁት መሢሕ መጣ አልተቀበሉትም ጠላት ገድሎ ነጻ ያወጣናል ብለው የጠበቁትን መሐሕ ሰቀሉት ገደሉት ቁርአኑ ደግሞ ኢየሱስ መሐሑ ነው ብሎ ተቀበለ ነገር ግን አልተሰቀለም አልተገደለም አለ ክርስትና ግን እንደ ሙስሊሞቹ የኢየሱስን መሐሕነት ተቀበለ አይሁድ እንዳመኑትም መሰቀልና መሞቱን ሲያምን ከዚህም በላይ መነሣቱንም አመነ አንባቢ ሆይ ልብህን የሚያሳርፈው እውነቱ ታዲያ የቱ ነው?

ሌላው በዚህ አንቀጽ ላይ የምናስተውለው ቁምነገር ኢየሱስ «በዚህ ዓለምና በመጨረሻውም ዓለም የተከበረ» መሆኑ ነው። ኢየሱስ በዚህ ዓለምና በሚመጣው ዓለም ፍጥረት ሁሉ ያከብረዋል ታዲያ ይህ ከሁሉ በላይ የሆነ እርሱ ማን ነው? ይህ ቃል ለማን ተብሏል? ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ የተነገረ ከሆነስ ምክንያቱ ምንድነው? ቁርአን እንኳ ስለ ክርስቶስ የሚከተሉትን እውነቶች ያምናል-

እርሱ ንጽሕት ከሆነች እናት የተወለደ ንጹሕ (ኃጢአት የማያውቅ) ነው (19፥19) እርሱ ብቻ በንጹሕ ድንግልና ያለ ወንድ ዘር ተወለደ እርሱ ብቻ «እኔ» እያለ አስተማረ «እኔ» እያለ ተአምራት አደረገ የሚጠበቀው መሢሕ እርሱ ሆነ እርሱ



www.ethiopianorthodox.org

በመጨረሻው ዓለም የተከበረው ብቸኛው መሒሕ ኢየሱስ እንዴት ነው ከባለሚሎቹ እንደ አንዱ የሆነ ልጅ የሚባለው? ከባለሚሎቹ በንጹሕ ድንግልና የተወለደ ኃጢአትንም የማያውቅ የለም ከአዳም ጀምሮ ሁሉ በደለኛ ነው ኢየሱስ ግን ንጹሕ ነው ስለ በደሉ ይቅርታ ያልጠየቀ ባለሚል ከርሱ በቀር አንድ እንኳ የለም:: አዳም ኃጢአት ሠርቷል (ሱረቱ 2፥ 36) አብርሃም ምሕረት ይጠባበቃል (ሱረቱ 26፥82) ሙሴ ምሕረት ለምኗል (ሱረቱ 28፥16) ዳዊት ይቅርታ ጠይቋል (ሱረቱ 38፥24) መሐመድ (ከባለሚሎቹ ባይሆንም) ኃጢአት ሠርቷል (ሱረቱ 47፥19) በቁርአን እንኳ «እኔ» ብሎ በሥልጣን የተናገረ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ከባለሚሎቹ ማን ነው? (አንቀጽ 49) ባለሚሎቹ ሁሉ የእግዚአብሔርን መንገድ አሳዩ ኢየሱስ ግን «እኔ መንገድ ነኝ» አለ (ዮሐ 14 ፥6) ፥ እርሱ እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ (ዮሐ 6፥48) ፥ የሕይወት ውኃ ነኝ (ዮሐ 7፥38) ፥ የሕይወት ብርሃን ነኝ (ዮሐ 8፥12) ፥ መልካም እረኛ ነኝ (ዮሐ 10፥11) የበጎች በር ነኝ (ዮሐ 10፥7) ፥ ብሎ አስተማረ በምድር ላይ ኃጢአትን ይቅር አለ (ሉቃ 5፥24 ፤ 7፥48) ፥ ስግደትን ተቀበለ (ማቴ 8፥2 ፤ ዮሐ 9፥38 ፤ ሉቃ 24፥52 ) ፥ እንዲህ ያስተማረ በሥልጣንስ ሁሉን ያከናወነ ከባለሚሎቹ የቱ ይሆን? አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ ያለ (ዮሐ 8፥ 58) ፥ የሞትና የሲኦል መክፈቻ በእጄ ነው ያለስ ከኢየሱስ በቀር የቱ ነቢይ ይሆን? (ራእ 1፥17 - 18) ፥ የነቢያቱን ሁሉ ትንቢት የፈጸመ (ሉቃ 24፥ 44፤ 25፥27) ፥ በፍቅር የሞተ ፥ በኃይል የተነሣ ፥ በክብር ያረገ ፥ በሥልጣንም



ለፍርድ (ለመፍረድ) የሚመጣ ከኢየሱስ በቀር ማን ነው? (ሉቃ 24 ፥46-51፤ ማቴ 28፥5 - 6፤ ማቴ 24፥30፤ ዮሐ 5፥27) እርሱ በድንግልና የሆነ ልደቱ ፥ ያለ ኃጢአት የሆነ ሕይወቱ ፤ በሥልጣን የሆነ ትምህርቱና ተአምራቱ፤ በሰውነቱ የሆነው ሞቱ ትንሣኤና እርገቱ እንዲሁም ገናና የሆነ ምጽአቱ (ለፍርድ መመለሱ) ልዩ ያደርገዋልና ከማንም ጋር አይነጻጸርም ድንግል ማርያም በመልአክ ብስራት የወለደችው ልጅ «ከባለሚሎቹ የሆነ ልጅ» ሳይሆን -

*«ሕፃን ተወልዶልናል ወንድ ልጅም ተሰጥቶናል አለቅነት በጫንቃው ላይ ነው ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘላለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል»* (ኢሳ 9፥6) ተብሎ እንደተጻፈ በስሙ ለሚያምኑት የልጅነትን ሥልጣን የሚሰጥ (ዮሐ 1፥12) ሥልጣኑ ለዘላለም የሆነ ልጅ ነው::

## 18. <u>የኢየሱስ ፈጣሪነት አዳኝነትና ሁሉን ዐዋቂነት</u>

### <u>አንቀጽ 49</u>

*«ወደ እስራኤል ልጆች መልእክተኛ ያደርገዋል /ይላልም/ እኔ ከጌታዬ ዘንድ በታምር መጣኋችሁ እኔ ለእናንተ ከጭቃ እንደወፍ ቅርጽ እፈጥራለሁ በሱም እተነፍስበታለሁ በአላህም ፈቃድ ወፍ ይሆናል በአላህም ፈቃድ እውር ሆኖ የተወለደውን ለምጸኛንም አድናለሁ ሙታንንም አስነሳለሁ የምትበሉትንና በቤታችሁ የምታደልቡትንም*



www.ethiopianorthodox.org

*ሁሉ እነግራችኋለሁ የምታምኑ እንደሆናችሁ ለእናንተ በዚህ ውስጥ በእርግጥ ታምር አለበት»*

ብዙ የቁርአን መልእክቶች በግኖስቲኮች ትምህርት ላይ የተመሠረቱ ናቸው ግኖስቲኮች በዘመኑ ትልቅ ሥፍራ የሚሰጠውን የግሪኮች የመጠቀ እውቀት ከእምነት ጋር ቀላቅለው የሰውን መዳን በእምነትና በእውቀት ላይ የመሠረቱ መናፍቃን ናቸው ፍልስፍናውን ከሃይማኖት ጋር አስማምተው ለመንዝ በሚያደርጉት ጥረት ብዙ የክህደት አስተምህሮዎችን ፈጥረዋል እንዲሁም ብዙ የተሳሳቱ መጽሐፍትንም ጽፈው ወደ ቤተክርስቲያን ለማስገባት ጥረዋል ::

ኢየሱስ ክርስቶስ ከጭቃ ወፍ ፈጠረ የሚለው ታሪክ የሚገኘው ግኖስቲኮች (ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የህፃንነት ዘመን የሚናገር የቶማስ ወንጌል) በሚል በሐዋርያው ቶማስ ስም ጽፈው ከአሰራጩት ወንጌል ነው የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት /ፈጣሪነት/ ያልተቀበለው መሐመድ ይህን ታሪክ ስለሰማው መጻፉ ለኛ ፋይዳ ባይኖረውም የቁርአኑን ሰዎች ብዙ ጥያቄዎችን ለመመለስ ያስገድዳቸዋል::

በአንቀጹ ውስጥ :-

* ወደ እስራኤል ልጆች እንደተላከ
* ከጌታ ዘንድ በተአምር እንደመጣ
* ከጭቃ ወፍ እንደፈጠረና በእርሱ እስትንፋስ በአላህ ፈቃድ ወፍ እንደሆነ
* እውር ሆኖ የተወለደውን ለምጻኛንም እንዳዳነና ሙት እንዳስነሣ



* በቤታቸው የሚመገቡትንና የሚያደልቡትን ሁሉ እንደሚያውቅ ተገልጿል::

«ወደ እስራኤልም ልጆች መልክተኛ ያደርገዋል (ይላልም):- እኔ ከጌታዬ ዘንድ በታምር መጣሁዋችሁ ... » ከሚለው ቃል ውስጥ-

1. «ወደ እስራኤል ልጆች መልክተኛ ያደርገዋል» የሚለውንና
2. እኔ ከጌታዬ ዘንድ በታምር መጣሁላችሁ የሚለውን ቃል እናስተውል::

<u>«ወደ እስራኤል ልጆች መልክተኛ ያደርገዋል»</u> የሚለውን ቃል በመያዝ አንዳንድ የዋህ ሙስሊሞች ኢየሱስ ክርስቶስ ለአንድ ወገን እንጂ ለዓለም ሕዝብ አልተላከም ሲሉ እንሰማለን ለዚህም አሳባቸው ማጠናከሪያ ወንጌል ይጠቅሳሉ ይኸውም ጥቅስ በማቴዎስ ወንጌል ም 15÷21 - 28 ያለው ነው:: ኢየሱስ ወደ ጢሮስና ሲዶና አገር በመጣ ጊዜ አንዲት ከነናዊት ሴት መጥታ ልጇን ከሚያሰቃየው ጋኔን እንዲፈውስላት ለመነችው ጌታ ግን ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጐች እንደተላከ ተናግሮ የልጆችን እንጀራ ለቡችሎች መጣል አይገባም ሲል እንደመለሰላት እናነባለን:: ሴቲቱ ግን ቡችሎችም ከጌቶቻቸው ማዕድ የወደቀውን ፍርፋሪ ይበላሉ ባለች ጊዜ ኢየሱስ የእምነቷን ታላቅነት መስክሮ ልጇን እንደፈወሰላት ተጽፏል::

የጌታችን መልስ የሴቲቱን ማንነት እንደሚገልፅ አለመረዳታቸውን በግልጽ እናያለን ጢሮስና ሲዶና በዓል የተባለው ጣዖት ይመለክባቸው የነበሩ አገሮች (ማቴ 11÷ 21) ሲሆኑ ከዚህ ከተማ የወጣችውም ሴት ዋነኛ የበዓል አምላኪ ከሆኑት ከነዓናውያን ወገን ነበረች ቁርአን ማጋራት የሚለው የጣዖት አምልኮ ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ውሻነት



www.ethiopianorthodox.org

መሆኑን ቁርአን ከተቀበላቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐቆች አንዱ መሆኑን ተመልክተናል ያደረጋቸው የነበሩትን ተአምራቶች ቀጥለን የምናጤናቸው ሲሆን አሁን ግን ወደ ተነሳንበት ኃይለ ቃል እንመልከት::

ኢሳ ወደ እስራኤል ልጆች ሄዶ ከጌታ ዘንድ መምጣቱን ነገራቸው ይህ ቃል በግልጽ እንደሚያሳየን ኢሳ ሰው ከመሆኑ በፊት ጌታ ዘንድ ነበረ «ዘንድ» የሚለው ቃል «ከ - ጋር» ወይም «አብሮ» ተብሎ እንደሚተረጎም ለሁላችንም ግልጽ ነው ስለዚህ ኢሳ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣ ቁርአን ከመሰከረ በርግጠኝነት ከመምጣቱ በፊት በጌታ ዘንድ (ከጌታ ጋር) እንደነበረ ቁርአን መስክሯል ስለዚህ የክርስቶስ ህልውና የሚጀምረው ከድንግል ማርያም ያለ ወንድ ዘር ከተጸነሰ ጀምሮ አይደለም ማለት ነው ይልቁንም ከፍጥረት ህልውና በፊት የነበረ ዘመናትን ወስኖ የሚኖር የዘመናት ጌታ ነውና «ከጌታዬ ዘንድ መጣሁ» የሚለው አገላለጽ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተብራርቶ እናገኘዋለን:-

«በመጀመሪያው ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ቃልም የእግዚአብሔርነበረ» (ዮሐ 1፥1) «ከጌታዬ ዘንድ» የሚለው የቁርአንን ንባብና «በእግዚአብሔር ዘንድ» የሚለው የዮሐንስ ወንጌል ንባብ ተቃራኒ አይደለም የመጽሐፍ ቅዱሱ ቃል ክርስቶስ ሰው ከመሆኑ በፊት ቃል እንደነበረ፣ በእግዚአብሔር ዘንድ እንደነበረና እግዚአብሔር እንደነበረ አብራርቶ ያስቀምጣል» በመጀመሪያ ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ» ሲል ግን ቁጥር 14 ላይ «ቃልም ሥጋ ሆነ» ስለሚል ሥጋ ከመሆኑ (ሰው ከመሆኑ) በፊት



የነበረ መሆኑን ለማስረዳት ነው ስለ ክርስቶስ ቃልነት አንቀጽ 45 ላይ በስፊው ተመልክተናል::

የክርስቶስ ከሰውነቱ በፊት መኖር (ዘላለማዊነት) በመጽሐፍ ቅዱስ በስፋት የተገለጸ ነው ጥቂቶቹን ለማየት

- *«ፈቃዴን ለማድረግ አይደለም እንጂ የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ ከሰማይ ወርጃለሁ»* *(ዮሐ 6 ፥ 38)*
- *እንግዲህ የሰው ልጅ አስቀድሞ ወደነበረበት ሲወጣ ብታዩ እንዴት ይሆናል? »* *(ዮሐ 6 ፥ 62)*
- «እውነት እውነት እላችኋለሁ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ አላቸው» (ዮሐ 8 ፥ 58)
- «አሁንም አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ» (ዮሐ 17 ፥ 5)
- «እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ አልፋና ዖሜጋ ፊተኛውና ኋለኛው መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ»
(ራእ. 22፥12 - 13)

እነዚህ ራሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተናገራቸው ጥቂቶቹ ሲሆኑ ሐዋርያቱም ይህን መስክረዋል-

*«እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም»*
*(ፊልጵ 2 ፥ 6)*

*«ከአብ ዘንድ የነበረውንም ለእኛም የተገለጠውን የዘላለምን ሕይወት እናወራችኋለን»* *(1ዮሐ 1 ፥ 2)*

*«ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘለዓለምም ያው ነው»*



www.ethiopianorthodox.org

*(ዕብ 13 ፥ 8)*

እነዚህ ምስክርነቶች ግልጽና እውነተኛ ምስክርነቶች ሲሆኑ ነቢያቱም ይህን ዘላለማዊ ዙፋን ያለው ዘላለማዊ አምላክ ከሩቅ በመንፈስ ተመልክተው መስክረውለታል፡-

/*መዝ* 44 (45) ፥6-7 ፤ *ዕብ* 1፥8-9 ፤ ኢሳ 6፥1-3፤ ዮሐ 12፥41፤ *መዝ* 73፥12፤ *ዳን* 7፥13-14/

በቱቂል ክፍል አንድ ላይ /2፣253/ ኢየሱስ ከሌሎች ነቢያት ከፍ ያለ እንደሆነና በግልፅ ተአምራቶች እንደተገለጠ አይተናል ባለፉት አንቀጾች ላይ ደግሞ እንዳየነው ኢየሱስ በድንግልና የተወለደ ከመሆኑ ጀምሮ ልዩ የሚያደርጉትን ምልክቶችና እርሱን ሰው ወይም ከነቢያት አንዱ ብቻ ነበረ እንዳንል የሚያስችሉንን የቁርአን አሳቦች አይተናል

ቁርአኑ ግልጽ ተአምራቶች ያላቸው ከላይ እንደዘረዘርነው የመጀመሪያው የኢየሱስን ፈጣሪነት የሚያሳየው አሳብ ነው እኔ ለእናንተ ከጭቃ እንደወፍ ቅርጽ እፈጥራለሁ በርሱም እተነፍሳለሁ በአላህም ፈቃድ ወፍ ይሆናል ትምህርቱ ከየት እንደተወሰደ ቀድመን ያየን ሲሆን እኛ ቁርአን የተቀበለውን እውነታ እንመዝናለን፡፡ ቁርአን ፈጣሪ ብቻ መፍጠር እንደሚችል-

*«ይኻችሁ ጌታችሁ አላህ ነው ከእርሱ በቀር አምላክ የለም ነገርን ሁሉ ፈጣሪ ነው»* (ሱ. 6 ፥ 102)



*« (የሚፈጥር) እንደማይፈጥር ነውን? አትገሰጹምን?»* (ሱ. 16፣17) በማለት ከአምላክ በቀር መፍጠር የሚችል እንደሌለ ያስረዳናል አምላክ ለማንም ይህንን ስልጣን እንደማይሰጥ /እንደማያጋራ/ ደግሞ፡-

*«እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትገዟቸው (ጣኦታት) ዝንብን ፈጽሞ አይፈጥሩም ለሱ (ለመፍጠር) ቢሰበሰቡም እንኳን (አይችሉም) አንዳችንም ነገር ዝምቡ ቢነጥቃቸው ከእሱ አያስጥሉትም»* በማለት ዝንብን እንኳ መፍጠር የሚችል አለመኖሩን በጽኑ ያስረዳል፡፡ ይኸው ቁርአን ነው እንግዲህ ኢሳ ከጭቃ የወፍ ቅርጽ እንደፈጠረና አላህ ስለፈቀደ በትንፋሹ ወፍ አደረገ (ሕይወት ሰጠ) የሚለን፡፡ የወፍ ቅርጽ እፈጥራለሁ የሚለው አገላለጽ ግልጽ አይደለም መፍጠር የሌለ አዲስ ነገር ማስገኘት ማንም ያላደረገውን (ሊያደርግ የማይችለውን) ማድረግ ማስገኘት እንጅ ያለን ነገር ማስመሰል (አስመስሎ መሥራት) መፍጠር ሊባል አይችልም ህፃናት ጭቃ እየጠፈጠፉ የሚሠሩትን የወፍ ቅርጽ ከሆነ የሠራው ኢሳ እፈጥራለሁ ማለት የለበትም ምክንያቱም ይህ ፈጠራ አይባልም ለኢሳ የተሰጠውና ግልጽ ተአምራት የተባለው ይህ ከሆነና እርሱም እፈጥራለሁ ካለ ከአፈር የተፈጠረው ሰው አዳም ነፍስ እስኪዋሃደው ድረስ ሙሉ አካል ያለው (የነበረው) በድን እንደነበረ ሁሉ (ዘፍ. 2 ፥ 7) የኢሳ ተአምራዊ የወፍ ፍጥረትም ከጭቃ የተቀረፀች ነገር ግን ሙሉ አካል ያላት በድን ወፍ ልትሆን ግድ ነው፡፡



www.ethiopianorthodox.org

መፍጠር ካልቻለ ግን ቀድሞውኑ የፈጣሪን ሥራ ወስዶ አፈጥራለሁ ማለት የለበትም ይህ እንደ ቁርአኑ አምላክን መጋፋት ነውና ተዓምራትም ከጭቃ ቅርጽ መፍጠር ሳይሆን ከጭቃ ልዩ አካል መፍጠር ነውና አንድ ህፃን የሚሠራውን የጭቃ ወፍ ቅርጽ ባለተአምራቱ ኢሳ ክሠራ የአላህ ቃልና መንፈስ የሆነው ፣ በዚህና በመጨረሻው ዓለም የተከበረው ፣ እንዲሁም ባለልዩ ተአምራቱና ኃጢአት የማያውቀው ኢሳ ከደካማውና ከኃጢአተኛው ሰው በምን ተለየ? አላህ ዝምብ መፍጠር አትችሉም እያለ ኢሳ የወፍ አካል የሚፈጥረው ምን ስለሆነ ነው ? በእርግጥ አምላክ ስለሆነ ነው::

ቀጣዩ ተአምራት ደግሞ ኢሳ በሠራት ወፍ ላይ ትንፋሹን መተንፈሱ ነው:: ምክንያቱም በድን የሆነችውን ወፍ እንድትበር ሕይወት ሊዘራባት ይገባል ይህ ሕይወት የመስጠት ሥልጣን ደግሞ በኢሳ እጅ ነው:: ከዚያም በርሱ ትንፋሽ ወፍዋ ወፍ ሆናለች (በራለች) በውኑ ይህንን ተአምራት ከነቢያት የሞከረ እንኳን በቁርአን በመጽሐፍ ቅዱስም ውስጥ የለም ያደረጉትን ሁሉ ያደረጉት ወደ እግዚአብሔር ለምነው ምላሽ ጠብቀው ነው ኢየሱስ ግን ሁሉን በስልጣኑ እኔ እፈጥራለሁ እያለ መናገሩን ልብ ማለት ይገባል አልፈጠረም ለማለት አንዳንድ ሙስሊሞች የሚያነሱት መከራከሪያ አለ ይኸውም በአላህ ፈቃድ የሚለውን ቃል ነው ቁርአን ሁሌ እራሱን /አንዱን አንቀጽ/ ለመከላከል በሚያነሳው ሌላ አሳብ /አንቀጽ/ ያልታሰበ ችግር ውስጥ ሲገባ ብዙ ጊዜ አይተናል:: በቁርአን ውስጥ



አንዱ አንቀጽ ሌላውን አንቀጽ የመሻር ነጻነት በብዛት የሚታየው ከችግር ለመውጣት በሚያደርገው መፍጨርጨር ምክንያት ነው ::

ኢየሱስ የወፍ ቅርጽ ፈጠረ በእርሱም ተነፈሰ እንጂ ወፍ የሆነው በአላህ ፈቃድ ነው የሚል ክርክር ተደጋግሞ በቁርአኑ ሰዎች ይነሳል:: ይህ አባባል ሙስሊሞች ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያስገድዳቸዋል ይኸውም -

1. አላህ ስለ ፈቀደ የኢሳ እስትንፋስ ለወፍ ቅርጽ ሕይወትን ሰጠ የሚል አስተሳሰብ ከሆነ ያላቸው አሁንም ሌላ ጥያቄ እንጠይቃለን አላህ ፈቅዶ ፈጣሪነትን ለኢሳ ሰጥቷል ማለት ነው? ከሆነስ መለኮታዊው የፈጣሪ ባሕርይ ይከፈላልን?
2. አይደለም የኢሳ ትንፋሽ ምንም ቦታ የለውም ቅርጹን ወፍ ያደረገው የአላህ ፈቃድ ብቻ ነው የሚል አስተሳሰብ ከያዙ አሁንም ሌላ ጥያቄ እናቀርባን ቀድሞ ቅርጽ እፈጥራለሁ እንዳለ ሁሉ አሁን ደግሞ በርሱም እተነፍስበታለሁ ለምን አለ? ለምን ተነፈሰበት? መፍጠርስ ከፈጣሪ በቀር የሚችል ማን ነው?

ታላቁ ነቢይ ረብ ጥቅም የሌለው ማስመሰል /ምትሃት/ ብቻ የሆነ ሥራ ይሠራልን? ከሆነስ ልዩውን ኢሳ መስደብ አይደለምን? ትንፋሹ ተአምራት ካላደረገ ጥቅም የሌለው ሥራ በመሥራት



www.ethiopianorthodox.org

የአምላክን ሥልጣን ከሚጋፋ ይህን ጭቃ ወፍ አድርግልኝ ብሎ መጸለይ አልነበረበትምን?

3. ከነቢያት በደረጃ ከፍ ያለ እርሱ ግልጽ ተአምራት ከተሰጠው ተአምራቱ ቃዲያ የቱ ነው? ተአምራት በምትሃት ማስመሰል ወይም የሰው ጥበብ ሳይሆን አምላካዊው ኃይል ብቻ የሚያደርገው አስደናቂ የሆነ እውነተኛ ድርጊት ነው።

በአላህ ፈቃድ የሚለው ቃል ኢሳ የራሱ ፈቃድ የለውም ወይም አላህ ካልፈቀደ ምንም ማድረግ አይችልም ለማለት የገባ ቃል ነው አምላክ ፈጣሪነቱን ፈቅዶ እንደማያውስ እላይ ያየነው አሳብ እንዳለ ሆኖ ኢሳ እንዴት ከአምላክ የተለየ ፈቃድ ይኖረዋል? በቁርአን ሦስት ሲል ሦስት አካል ብቻ ሳይሆን ሦስት ፈቃድ ጭምር ያለ ስለሚመስል ይህ ግጭት ይፈጠራል (ሥላሴን በተመለተ ቀጣዩን የቁርአን ምዕራፍ በምናይበት ቁጥር 3 መጽሐፍ ላይ በሰፊው እናየዋለን) በክርስትና የአንድ አምላክ አምልኮ ውስጥ ሦስቱ አካላት የማይለወጥ አንድ ዘላለማዊ ፈቃድ ያላቸው በመሆኑ ይህ ግጭት አይኖርም ኢየሱስ ከአብ የተለየ ፈቃድ ቢኖረው ልክ ቁርአኑ እንደሚለው ሁለት ወይም ሦስት አምላክ እንደምናመልክ በተቆጠረ ነበር። በአላህ ፈቃድ ወፍ ይሆናል የሚለው አነጋገር አላህ ወፍ ያደርገዋል ማለት ሳይሆን የኢሳ እስተንፋስ ሕይወት ሰጠው



እንዲህም እንዲሆን የአላህ ፈቃድ ሆነ ማለት እንደሆነ ለማንም ግልጥ ነው። ቃሉን በነጻ አእምሮ የሚመለከት ሁሉ እንደዚህ የሚረዳ ሲሆን በዚህም ኢሳ ፈጣሪ መሆኑን ያለ አንዳች ማወላወል ሊቀበል ይችላል። ምክንያቱም ተአምራቶቹ አምላካዊ /መለኮታዊ/ ሥራዎች ናቸውና።

*«ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች እንኳ ያለ እርሱ አልሆነም»* *(ዮሐ. 1 ፥ 3)*

*«እኔ የአባቴን ሥራ ባላደርግ አትመኑኝ ባደርገው ግን እኔን እንኳን ባታምኑ አብ በእኔ እንደሆነ እኔም በአብ እንደሆንሁ ታውቁና ታስተውሉ ዘንድ ሥራውን እመኑ»* *(ዮሐ 10 ፥ 37 - 38)*

*«እኛ ፍጥረቱ ነንና እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን»* *(ኤፌ 2 ፥ 10)*

*«እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው የሚታዩትና የማይታዩትም ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው ሁሉ በርሱና ለርሱ ተፈጥሮአል እርሱም ከሁሉ በፊት ነው ሁሉም በእርሱ ተጋጥሟል»* *(ቆላ 1 ፥ 15 - 17)*



www.ethiopianorthodox.org

ቢባልም አሁን ግን ዕርም አይደለምና ማድረግ /መፈጸም/ ትችላላችሁ ለማለት/ መጣሁ አለ። እፈቅድ ዘንድ መጣሁ በማለት የሕግ ባለቤት /ሕግ ሠሪ/ እንደሆነ በነገር ሁሉ ላይ ሥልጣን እንዳለው አረጋገጠ። አንባቢ ሆይ ታዲያ ክርስቶስ ማን ነው? ባለፈው አንቀጽ ላይ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት በግልጽ የሚያስረዱ ታምራቶቹን ስንመለከት እርሱ እኔ እያለ ያለ መከልከል ድንቅ/ ማንም ሊያደርግ የማይችላቸውን/ ታምራት ያደርግ እንደነበር ሁሉ አሁን ደግሞ በሕግ በተደነገጉ ዕርም የሆኑና ያልሆኑ ነገሮች ላይ ፈቃጅና ከልካይ መሆኑን እፈቅድ ዘንድ መጣሁ በማለት በሥልጣን ተናገረ/ ለምሳሌ በቁርአን ላመኑ ሙስሊሞች ዕርም የተደረጉ ነገሮች /በሱ. 2 ፥ 172 - 173/ *«እናንተ ያመናችሁ ሆይ ከነዚያ ከሰጠናችሁ ጣፋጮች ብሉ ለአላህም እርሱን ብቻ የምትገዙ እንደሆናችሁ አመስግኑ በናንተ ላይ እርም ያደረገው በክትንና ደምን የእርያ ሥጋንም በርሱም /ማረድ/ ከአላህ ስም ሌላ የተነሣበትን ነገር ብቻ ነው ሺፍታና ወሰን አላፊ ሳይሆን /ለመብላት/ የተገደደ ሰውም በርሱ ላይ ኃጢአት የለበትም አላህ መሐሪ አዛኝ ነውና»* /በማለት ይገልፃቸዋል:

እነዚህ እርም የተደረጉ ነገሮች የበከተ /የሞተ/ ፥ ደም፣ የእርያ ሥጋ እንዳይበሉ በአላህ ስም ያልታረደ እንዳይመገቡ የከለከለ አላህ ነው፣ የእርያ ሥጋ እንዳትበሉ የሚለው የብሉይ ኪዳን ሕግ ሲሆን ቀሪዎቹ ግን በሐዲስ ኪዳን ላይ በሐዋርያት ሲኖዶስ ቀድሞ የተወሰኑ



ናቸው:: /የሐዋ 15 ፥ 28 - 29/ ከሐዋርያት ውሳኔ እዚህ ውስጥ ያልተካተተው ከዝሙት ራቁ የሚለው ብቻ ነው::

አላህ እላይ የተዘረዘሩትን ብቻ ሳይሆን እርም ከሆኑት ሌላ የፈቀደው አንድ ነገር አለ እርሱም ቀድሞ ሌባ ያልነበረ ሰው ቸግሮት ቢሰርቅና ቢበላ ኃጢአት አይሆንበትም እኔ መሐሪ አዛኝ ነኝ ብሏል፣ ይህ ጻድቅ ከሆነው አምላክ ባሕርይ ጋር የማይሄድ ባይሆንም እርሱ/ አላህ/ ከልካይ ስለሌለው እንደወደደ ያደርጋል ነገር ግን ይህ ሕግ ብዙ ቦታ ሊጠቀስና ብዙ ጥፋት ሊጠፋ እንደሚችል መገመት አያዳግትም::

ዋናው ነጥብ አላህ /እንደ አምላክ/ እርም ሲያደርግና ሲፈቅድ እንደበረ ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ ከዚህ በላይ ቀድሞ እርም የተባሉ /የተከለከሉ/ ነገሮችን ሊፈቅድ መምጣቱን ተናገረ እነግዲህ ይህ የፍጡር ወይስ የፈጣሪ ባሕርይ?

## 20. ጌታዬና ጌታችሁ

## አንቀጽ 51

*«አላህ ጌታዬና ጌታችሁ ነው ስለዚህ ተገዙት ይህ ቀጥተኛው መንገድ ነው አላቸው»*

ይህን የቁርአን ጥቅስ የሚያነብ ሙስሊም ሁሉ ኢየሱስ ጌታ አለው ወይም ፍጡር ነው ሊል በቀላሉ ይደፍራል ይህ በራሱ እስከ አሁን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ካየናቸው እውነታዎች ጋር የሚጋጭ ሲሆን ተመሳሳይ ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ እየተጠቀሰ እኛንም /ክርስቲያኖችን/



www.ethiopianorthodox.org

በዘመናት ሦስት አምላክ ብለው እንደማያውቁ ለሙስሊሞች ማረጋገጥ እንወዳለን። በአንቀጽ 49 ላይ በሰፊው ያየናቸው ግልጽ ምልክቶች /ታምራቶች/ የኢየሱስ ክርስቶስን ጌትነት የሚያረጋግጡ መሆናቸውን ተመልክተናል ።

1. «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት»

ሲል «አባት» የሚለውን ቃል አይቀበሉትም ምክንያቱም አብን ከተቀበሉ /ወልድን/ ይቀበላሉና ወልድን ከተቀበሉ ሥላሴን ተቀበሉ አመኑ ማለት ነው። ይህ ለብዙዎቹ ከባድ ቢሆንም ነገር ግን የዘላለም ሕይወት መንገድ ነው።

*«እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንክ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት»* (ዮሐ 17 ፥ 3)

አብንና ወልድን ማወቅ /ማመን/ የዘላለም ሕይወት እንደሆነ ቃሉ ሲያረጋግጥ የዘላለም ሕይወት ከአንዱ ጌታ በቀር ማንም የለምና አምላኬ አምላካችሁ ጌታዬ ጌታችሁ ሲል ለኛ አንድ ጌታ /አምላክ/ ብቻ መኖሩን ግልጽ ነው። እንዲሁም አባቴ ሲል —

*«አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ በማለት እንዳስተማረን ወልድ ዓለም ሳይፈጠር በአብ ዘንድ የነበረው ክብር ፈጣሪነት ነው* (ዮሐ 17፥5፣ ዮሐ. 1 ፥ 1)



ስለዚህ ልጅነቱ የፍጡር አእምሮ መርምሮ የማይደርስበት በዘመን መቀዳደም በክብር መበላለጥ የሌለበት ዘላለማዊ ልጅነት ነው ተፈጥሮአዊውን የመዋለድ ሕግ ለቅጽበት እንኳ እንዳታስብ ነገር ግን ልጅ አባቱን እንዲመስል ወልድ አብን በመለኮታዊ ባሕርይ የሚመስለው እንዲሁም በልጅና በአባት መካከል እንዳለው ባሕርያዊ አንድነትና ቀረቤታ በመካከላቸው መኖሩን የሚያሳይ ቃል ነው ፍጡር ፈጣሪን መርምሮ ቢደርስበት ፈጣሪ አይኖርም ነበር።

ታዲያ በቁርአን ያለው /ጌታዬና ጌታችሁ/ የሚለው የአዲስ ኪዳን ንግግር ምን ማለት ሊሆን ይችላል? የጥያቄውን ተገቢነት ለማጉላት በሌላ ምዕራፍ የተጠቀሰውን ተመሳሳይ የኢሳ ንግግር እንመልከት።

*«እነዚያ አላህ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ነው ያሉ በእርግጥ ካዱ አልመሲሕም አለ የእስራኤል ልጆች ሆይ ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ»* (አል-ማኢዳህ 5 ፥ 72)

*«በርሱ ያዘዝከኝን ቃል ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ ማለትን እንጂ ለነርሱ ሌላ አላልኩም»* (አል-ማኢዳህ 5 ፥ 117).

በሁለቱም የተለያዩ አንቀጾች ላይ ኢሳ በንግግሩ ጌታዬና ጌታችሁ ሲል እንሰማዋለን በአንቀጽ 49 ላይ ኢሳ አደረጋቸው የተባሉት ተአምራት አስቀድሞ በመጽሐፍ ቅዱስ በዝርዝር የተጻፉና ኢየሱስም ጌትነቱን ያስረዳባቸው ሲሆኑ በቁርአን ላይ ደግመው ከተጻፉ ጌታዬና ጌታችሁ የሚለው ንግግርም አምላኬና አምላካችሁ ከሚለው ክርስቶስ በወንጌል ከተናገረው ቃል በቀጥታ የተወሰደ ሊሆን ይችላል ስለዚህ



www.ethiopianorthodox.org

ምስክርነታቸው እውነት ነው ሐዋርያቱ አብረውት እንደነበሩም ቁርአን ራሱ አረጋግጧል (አንቀጽ 52 ተመልከት)

እስከ አሁን የተናገርነው ታሪክ ቀጣይ በዚህ አንቀጽ ላይ አላህ ኢሳን የተናገረው ንግግር ነው ይኸውም «እኔ ወሳጂህ ወደኔም አንሺህ ነኝ» ይላል አይሁድ አደሙ አላህ አድማቸውን መለሰባቸው ሲል ኢየሱስ ክርስቶስን ሊይዙት ሊያንገላቱት ሊሰቅሉትን ሊገድሉት አልቻሉም ማለት ነው ምክንያቱም አላህ አልፈቀደምና ቅዱሳኑ (ነቢያቱ) መከራ እንዲቀበሉ አላህ አይፈቅድም ማለት ነው? ከአቤል ጀምሮ የብዙ ቅዱሳን ደም በማን ፈቃድ ፈሰሰ? ቁርአን ራሱ ጠሱ 2÷ 87 - 154 ላይ -

*«...ነፍሶቻችሁ በማትወደው ነገር መልክተኛ በመጣላችሁ ቁጥር (ከመከተል) ትኮራላችሁን? ከፊሉን አስተባበላችሁ ከፊሉንም ትገድላላችሁ»*

*« በአላህ መንገድ (ለሃይማኖት) የሚገደሉትን ሰዎች ሙታን ናቸው አትበሉ በውነቱ ሕያዋን ናቸው ግን አታውቁም»*

እውነትን ተሸክሞ ያልተሰደደ በድንጋይ ያልተወገረ በመጋዝ ያልተተረተረ ለእሳትና ለአራዊት ያልተጣለ ማን ነው? አላህ እነዚህን ለምን አልሰወረም? ለምንስ ወደርሱ አላነሳቸውም? ዋጋ ካልከፈሉበት እውነት እንዴት ይከበራሉ?

ምርጦቹ ዓለም የምታቀርበውን የመከራ ፅዋ ጨልጠው ዓለምን ያሳፍራሉ እንጂ የታመኑበትን ጌታ በመከራ ብዛት ክደው አያሳፍሩም መከራቸው የክብር አክሊል የሚቀዳጁበት መንገድ ነው አምላክም መከራውን ሳይሆን የሚያሳልፈው መከራውን የሚያልፉበትን ጸጋ ነው የሚያበዛላቸው::



*« ... ጸጋዬ ይበቃኋል ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና አለኝ»*
(2ቆሮ 12 ÷ 7 -10)

*«...ትታገሱም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያዘጋጃል»* (1ቆሮ 10 ÷ 13)

*« ... ጻድቅ ግን በእምነት ይኖራል ወደ ኋላም ቢያፈገፍግ ነፍሴ በእርሱ ደስ አይላትም»* (ዕብ 10 ÷ 38)

*« ... ወደ እግዚአብሔር መንግስት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል»* (የሐዋ 14 ÷ 22)

ታዲያ ኢየሩሳሌምን በአንድ እግሯ ያቆማት የአይሁድን አድማ ጸጥ እረጭ አድርጐ ኢሳን ወደሰማይ የሚወስድበት ምክንያት ምንድነው? ኢሳ ከርሱ በፊት እንደሞቱት እንደ ብዙዎቹ እንዳይሞት አላህ «ወደኔ ወሳጂህ ነኝ» ያለበት ምክንያት ምንድነው? «ወደእኔ አንሺህ ነኝ» ሲልስ የተዘለለ ታሪክ ያለ አይመስልህም? ይህውም ሞቱ ነዋ? ምክንያቱም ያልሞተ እንዴት ይነሳል? ትንሣኤ ካለ ሞት አለ በአራቱም ወንጌላት በሙላት የተረጋገጠው የክርስቶስ ሞት ያለ ግልጽና በቂ ምክንያት በቁርአን ተዘሏል አንባቢ ሆይ! ክርስቶስ ሙታንን ሲያስነሳ በቁርአን አይተናል እርሱ ግን በፈቃዱ ሞቷል ሞቱም ለኃጢአታችን ያለኃጢአት የተከፈለ የፍቅር ዋጋ ስለነበር ቤዛችን ሆኗል ብታምን ላንተም የቆመ ማስተሥርያ ነው:: (ስቅለቱንና ሞቱን በተመለከተ በቀጣዩ መጻፍ በሰፊው እናየዋለን)

በዚህ አንቀጽ ውስጥ ሌላው ነጥብ *«እነዚያን የተከተሉህን እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስ ከነዚያ ከካዱት በላይ አድራጊ ነኝ»* የሚለው ነው የትንሣኤ ቀን የፍርድ ቀን ሲሆን በዓለም ላይ ለመፍረድ የሚመጣው



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቶስ መሆኑን ልክ እንደ ክርስትናው እስልምናውም ያምናል ይጠብቃል:: ግን ለምን? ከነቢያት አንዱ የሆነው ክርስቶስ የመፍረድ ሥልጣን ለምን ተሰጠው? አሁንም በእስልምናው ይህ መልስ የሌለው ጥያቄ ነው:: በመ/ቅዱስ ግን-

*«የሰው ልጅም ስለሆነ ይፈርድ ዘንድ ሥልጣን ሰጠው»*

(ዮሐ 5፥27) ይላል::

«የሰው ልጅም ስለሆነ» ሲል በሰውነቱ ሞትን ስለቀመሰ ዋጋ ስለከፈለ በዚህ ዋጋ ለተገዙት ይፈርድላቸዋል ባላመኑት ደግሞ ይፈርድባቸዋል ማለት ነው መከራ አለመቀበሉና አለመሞቱ ሲገርመን ፈራጅ ነህ መባሉ ደግሞ የበለጠ ጥያቄ ውስጥ ይከተናል:: በድንገተኛ ህመም ቢሆንም የሞተው የነቢያት መደምደሚያ ነው የሚባለው መሐመድ መፍረድ አልነበረበትም? ብለን እንድንጠይቅ እንሆናለን:: ከክርስቶስ ትንሣኤ ጋር ተያይዞ የትንሣኤ ቀን (የሙታን መነሳትና የፍርድ ቀን) መወሳቱ ክርስቶስ ሞቶ በመነሳትና ለዘላለም ሕያው ሆኖ በመኖር የትንሣኤ በኩር (ጀማሪ) ባይሆን ነውን? ብለን እንድንጠይቅ እንገደዳለን:: ከዚህም ሁሉ ጋር «እነዚያን የተከተሉህን እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስ ከነዚያ ከካዱት በላይ አድራጊ ነኝ» ሲል የክርስቶስ ተከታዮች ክርስቲያኖች መሆናቸውን ቁርአን ደግሞ ያረጋግጣል የካዱት ደግሞ ያደሙበት አይሁዶች መሆናቸውም የተገለጸ ሲሆን የክርስቶስን ተከታዮች ከከሃዲዎች በላይ መደረጋቸው ተገልጿል::

በሌላ አነጋገር ክርስትና ከይሁዲነት በላይ መሆኑ ተረጋግጧል «እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስ» ሲል ከትንሣኤ (ከፍርድ ቀን) በኋላ ልዩ ልዩ የሃይማኖት ሥርዓት ስለማይኖር ፍፃሜ የሌለው «እስከ» ነው ማለት ነው ስለዚህ ቁርዓን የክርስትናን ዘላለማዊ ልዕልና /ታላቅነት/



በማያሻማ ምስክርነት ተቀብሏል:: ለፍርድ ቀን የሚገለጠው ኢየሱስ መሆኑን ማመን አያድንም ይልቁንም ክርስቶስ «ሊፈርድ» የሚመጣው ስለ ዓለም ኃጢአት ዋጋ በመክፈሉ ነው ብሎ ማመንና የዚህ እውነት (ክርስትና) ተከታይ መሆን የትንሣኤ ቀን የበላይነትን እንደሚያጎናጽፍ አንዳች ጥርጥር የለውም::

*«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና:: በርሱ በሚያምን አይፈረድበትም በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል»*

(ዮሐ 3 ፥ 16 - 18)

## 23. <u>ሰው ከየትኛው ተፈጠረ? ዒሳ የአዳም ብጤ ወይስ...?</u>
## <u>የሚጣረሰው አንቀጽ 59</u>

*« አላህ ዘንድ የዒሳ ምሳሌ እንደ አዳም ብጤ ነው ከአፈር ፈጠረው ከዚያም ለርሱ (ሰው) ሁን አለው ኾነም»*

በዚህ አንቀጽ ላይ አዳም ለኢሳ ምሳሌ (ብጤ) ሆኖ ቀርቧል የዚህን አሳብ ትክክለኛ መሆንና አለመሆን ከመመርመራችን በፊት ስለ ሰው አፈጣጠር በቁርአን የተዘገበውን የተራራቀ መረጃ እንመልከት:: በዚህኛው አንቀጽ ላይ ለክርስቶስ ብጤ ነው የተባለው አዳም-

1. ሱ 3 ፥ 59 - «ከአፈር ፈጠረው»



www.ethiopianorthodox.org

*«ይህ እርሱ በርግጥ እውነተኛ ታሪክ ነው አምላክም ከአላህ በስተቀር ምንም የለም አላህም እርሱ በርግጥ አሸናፊው ጥበበኛው ነው»*

ከዚህ አንቀጽ በፊት ያየነው «የኢሳ ምሳሌ እንደ አዳም ብጤ ነው» የሚለው ክርስቶስ ኢየሱስን ፍጡር የሚያደርገው የመሐመድ ትምህርት ተቀባይነት ያላገኘና ተቃውሞ የገጠመው መሆኑን ይህ አንቀጽ ያሳያል «ዕውቀቱ ከመጣልህ በኋላ በርሱ (በኢሳ) የተከራከሩህን ሰዎች» የሚለው ሐረግ ኢሳ እንደ አዳም ነው የሚለውን ትምህርት (ዕውቀት) ያልተቀበሉ ሰዎች መኖራቸውን ሲያሳይ እነዚህም ሰዎች ስለ ክርስቶስ ማንነት አስቀድሞ ዕውቀት የነበራቸው ክርስቲያኖች መሆናቸው አያጠራጥርም። መሐመድ ትምህርቱን በአብዛኛው ከክርስትና አፈንግጠው በተቃራኒ ጐን ከቆሙ መናፍቃንና ግኖስቲካውያን ያገኘው መሆኑን በቴቄል ክፍል 1 ላይ የተመለከትን ሲሆን ቤተ ክርስቲያን ወልድ ፍጡር ነው ካለ ከአርዮስ ጀምሮ ሁሉንም መናፍቃንና መጽሐፍ ጠቅሳ ተከራክራ ረትታ ባለመመለሳቸው ለይታቸዋለች ስለዚህ ይህ የመሐመድ ትምህርት ከ7ኛው መቶ ክ/ዘመን በፊት ቤተ ክርስቲያን ብዙ ጊዜ የሰማችው የሰይጣን ትልቁ ዓላማ ሲሆን የተመሠረተችው ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነው (እግዚአብሔር ነው) በሚለው ምስክርነት ላይ ስለሆነ አልተናወጠችም።

መሐመድ ክርስቶስ የአዳም ብጤ ነው ለሚለው ትምህርቱ አይደለም የአዳም ፈጣሪ ነው የሚለው የክርስቲያኖች ምላሽ የመጽሐፋቸው ትምህርት መሆኑን ስለማያውቅ (ስላልገባው) ክርክሩን ለሰዎች እንጂ ለመጽሐፋቸው አይሰጥም ይህ የክርስቶስ አምላክነት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሆኑን ቢያውቅ ኖሮ-

ሀ. መጽሐፍ ጠቅሶ ይከራከር ነበር አንድም ቦታ ይህን ለማድረግ አልሞከረም

ለ. ለክርስቲያኖች መመሪያ በዘመኑ ለነበረው መጽሐፍ ቅዱስ ትልቅ ክብርና ዕውቅና አይሰጥም ነበር።

ከዚህ ይልቅ መሐመድ የተከራከሩትን ክርስቲያኖች ልጆቻችንን ሚስቶቻችንን ነፍሶቻችንን ጠርተን አላህን እንለምን ከዚያም የአላህን ቁጣ በውሸታሞቹ ላይ እናድርግ በማለት ለቁጣ ይዘጋጃል። ላላመኑ ሰዎች ዕውቀትን እንዲገልጥ በፍቅርና በምሕረት መለመንን ቁርአን ውስጥ አናይም ልጆችንና ሚስቶችን ሰብስቦ መለመን ለተከራካሪ መልስ ይሆናልን? ይህ ልመና ምንም መልስ ሳያገኝ ምኞት ብቻ ሆኖ ይቀርና በቀጣዩ አንቀጽ ላይ «ይህ እርሱ በእርግጥ እውነተኛ ታሪክ ነው» በማለት ዓለም የዳነበትን እውነት ታሪክ አድርጐ ያስቀረዋል ማንም ቢሆን ከሌሎች የወሬ ወሬ የሰማው ነገር ለርሱ ታሪክ ነው። አንቀጹ በመቀጠል «አምላክም ከአላህ በስተቀር ምንም የለም» በማለት ክርስቲያኖቹ መሐመድን የተከራከሩት ኢየሱስ አምላክ (ፈጣሪ) ነው በማለት እንደሆነ ያሳየናል ነገር ግን መሐመድ ይህን አባባላቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛ የአንድ አምላክ እምነታቸው መሆኑ ስላልገባው መጽሐፋቸውን ሳይሆን የመጽሐፉን ሰዎች እውነትን እንደደበቁ አድርጐ በጅምላ ሲወቅስ እንመለከታለን።

ይህ የሚያረጋግጥልን እውነት አለ ይኸውም መሐመድ የክርስትና መመሪያ ለሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛነት እውቅና ከሰጠ ክርስቲያኖቹ ደግሞ እርሱ ራሱን ክርስቶስ አምላክ እንጂ ፍጡር





www.ethiopianorthodox.org

መሃል የተነሣ ነቢይነት የተሰጠው ሌላ ሰው ካልነበረ ከሱም በኋላ ካልተነሳ ይህ ተራ ክስ ብቻ ነው የሚሆነው:: ቁርአን አላህ አንድ ነው እያለ «አማልክቶች አድርጋችሁ እንድትይዙ ሊያዛችሁ አይገባም» ሲል አማልክቶች የሚባሉትን ከእውነተኛው አምላክ ጋር አንድ እያደረጋቸው መሆኑ ወይም ክርስቲያኖች ሦስት ስንል አማልክት (ሦስት አምላክ) እንደምንል በመቁጠር መሆኑ ግልጥ ነው:: አማልክት የሚለው ቃል ገገርዎች ወይም ጌቶች ማለት ሲሆን እግዚአብሔር በጸጋ ያደረባቸውንና ከሌሎች የለያቸውን (ያስበለጣቸውን) ቅዱሳን/ ነቢያትን ሐዋርያት... / መግለጽ የሚችል ቃል ነው እግዚአብሔር ከነዚህ ሲለይ «የአማልክት አምላክ» ይባላል ሁለቱ ልዩነቶች በእንግሊዘኛው እውነተኛው አምላክ (እግዚአብሔር) “God” ሲባል ከዚያ ውጭ ያሉት ደግሞ “gods” ተብለው ይጠራሉ:: መሐመድ በካዕባ ውስጥ ይመለኩ የነበሩ ብዙ አማልክት (ጣዖታትን) አጥፍቶ ታላቁን የጨረቃ አምላክ የተባለውን ጣዖት አላህን ብቻ በማስቀረት ብጤ የለውም ብሎ ስላወጀ «አማልክት» ሲባል ሁሉን ቻዩ አምላክ ይመስለው እንደነበር ከቃሉ እንረዳለን::

*«እግዚአብሔር በአማልክት ማህበር ቆመ*
*በአማልክትም መካከል ይፈርዳል» (መዝ 81(82)÷1)*
*«የአማልክትን አምላክ አመስግኑ» (መዝ 135(136)÷2)*

*«ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው:- እኔ አማልክት ናችሁ አልሁ ተብሎ በሕጋችሁ የተጻፈ አይደለምን? መጻፉ ሊሻር አይቻልምና እነዚያን የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን አማልክት ካላቸው የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ስላልሁ እናንተ አብ የቀደሰውን . . . » (ዮሐ 10÷34-36)*



*«እግዚአብሔርም ሙሴን አለው:- እይ እኔ ለፈርዖን አምላክ አድርጌሃለሁ» (ዘጸ 7÷1)*

## 27. በውድም በግድም የሚጣረሰው አንቀጽ 83

*«በሰማያትና በምድር ያሉ ሁሉ በውድም በግድም ለርሱ የታዘዙ ወደርሱም የሚመለሱ ሲኾኑ (ከሐዲዎች) ከአላህ ሃይማኖት ሌላን ይፈልጋሉን?»*

ዲያብሎስ ላይ መፍረዱ አዳምንም ከገነት ማባረሩ የተነገረለትና ለኃጢአተኞችም እሳትንና ብርቱ ቅጣቱን ያዘጋጀው አላህ የሰዎችን እና የመላእክትን ነጻ ፈቃድ በማክበሩ ወይስ ባለማክበሩ? ነፃነትን ስለሰጠ ነው የሚቀጣ? ወይስ በእርሱ ውሳኔ ጻድቅና ኃጢአተኛ ስለሆኑ? በእርግጥ ለዚህ ጥያቄ ቁርአን የሚሰጠው መልስ ሌላ ጥያቄ እንድናነሳ ሊገፋን ይችላል:: በዚሁ ምዕራፍ አንቀጽ 129 ላይ:-
በሰማይና በምድር ያለው ሁሉ በውድም በግድም ለርሱ ይታዘዛል ወደርሱም ይመለሳል የሚለው አንቀጽ በአንቀጽ 86 ላይ ከተጠቀሰው አሳብ ጋር ተቃራኒ ነው-

*«ከእምነታቸውና መልክተኛውም እውነት መሆኑን ከመሰከሩ የተብራሩ አንቀጾችም ከመጡላቸው በኋላ የካዱትን ሕዝቦች አላህ እንዴት ያቃናል አላህ በዳዮችንም ሕዝቦች አያቃናም»*

በሰማይም ሆነ በምድር ያሉ ሁሉ በውድም በግድም ለርሱ የሚታዘዙ ወደርሱም የሚመለሱ ሆነው ሳለ የመልክተኛውን ትክክለኛ ነት ከመሰከሩና የተብራሩ አንቀጾችን ከሰሙ በኋላ የካዱትን አላህ



www.ethiopianorthodox.org

ቁርአን በእስራኤል ምድር የተመረጡ አባቶችን የነገሡ ነገሥታትና የተቀቡ ነቢያትን በጂምላ ነቢያት ብሎ ሲጠራቸው እነዚህ ሁሉ ቅዱሳን የፈለቁባትን ኢየሩሳሌም ግን አንድም ጊዜ አያነሳትም ለምንድነው? ሁሉንም ነቢያት ካሳቸው በኋላ መሐመድን ነቢይ ብቻ ሳይሆን የነቢያት መደምደሚያ ይለዋል መሐመድ የነብያት መደምደሚያ ስለሆነ ደግሞ እርሱ የተነሳባት መካ የከተሞች ሁሉ እናት ተብላለች:: ለመጀመሪያ ጊዜ ቤተመቅደስ የተሠራውና ቋሚ የአምልኮ ሥርዓት የተጀመረው በሰሎሞን ዘመን ሲሆን የእግዚአብሔር ክብር መቅደሱን እስኪሸፍነውና ካህናቱ ማገልገል እስኪሳናቸው በክብር የተሞላውን መቅደስ እንኳ የመሳለም ግዴታ አልነበረም ከሰሎሞን በፊት መቅደስ አልነበረም ለሙሴ የተሰጠው የቃል ኪዳን ታቦት የነበረው በድንኳን ውስጥ ነበር ከሙሴ በፊት ደግሞ እንኳን መቅደስ ድንኳንም አልነበረም አብርሃምና ልጆቹ ሌሎቹም ቅዱሳን በየደረሱበት መሠዊያ እየሠሩ መሥዋዕት ያቀርቡ እግዚአብሔርንም ያመልኩ ነበር:: (ዘፍ. 12÷8፣ 13 ÷18፣ የሐዋ. 7÷44-47) ታዲያ የካዕባው ቤተ መቅደስ ከየት መጣ? ከአብርሃምስ ጋር ምን አገናኘው? በሴሎ የነበረው የመገናኛው ድንኳንና ታላቅ ክብር የነበረው የኢየሩሳሌም የሰሎሞን ቤተመቅደስ በመካ ባለው ካዕባ ቀደሚነታቸውን ተነጥቀዋል ሰዎች እንዲጸልዩበትና ለዓለማት መምሪያ እንዲሆን የመጀመሪያው መቅደስ በመካ ያለው ካዕባ ነው የሚለው አስተሳሰብ ምንም ዓይነት ታሪካዊ መረጃ የሌለው ጥቅምና ክብር ፍለጋ የሚደረግ የታሪክ ሽሚያ ነው::

መሐመድ ስለ መካና በውስጧ ስለሚመለከው አምላክ በቁርአን እንዲህ ብሎ ነበር-



*«የታዘዝኩት የዚችን አገር ጌታ ያንን ክልል ያደረጋትን እንድገዛ ብቻ ነው ነገሩም ሁሉ የእርሱ ነው ከሙስሊሞችም እንድሆን ታዝዣለሁ /በላቸው/:: »* (ሱረቱ 27÷91)

መሐመድና እስልምና ከመምጣታቸው በፊት መካና ካዕባ እንደነበሩ ሁሉ በዚያ ይመለክ የነበረው አላህም ነበር::

«የዚህችን አገር» የተባለችው መካ ስትሆን «የዚህችን አገር ጌታ» ማለትም የመካ ጌታ (አምላክ) ደግሞ አላህ ነው ይህ አላህ የጨረቃ አምላክ ሲሆን ሁባል በመባልም ይታወቅ ነበር:: ይህ እንግዲህ መሐመድ ከመነሳቱ በፊት ጀምሮ መካውያን ይከተሉት የነበረው ጣዖት አምልኮ መሆኑ ግልጥ ነው:: በተጨማሪም-

*«የዚህን ቤት /የካዕባን/ ጌታ ይገዙ»* (ሱረቱ 106÷3)

በማለት መሐመድ ብቻ ሳይሆን የርሱ ጕሳዎች ቁረይሾችም ሊገዙ የሚገባው ለካዕባው ጌታ /ለአላህ/ ብቻ መሆኑን ነግሮአቸዋል ካዕባ ውስጥ ለረጅም ዘመናት ሲመለክ የነበረው ደግሞ አላህ ነው:: የዚህ ቤት ጌታ ማለት የዚህ ቤት ባለቤት የዚህ ቤት ተጠሪ ማለት ነው/ ካዕባ እንደሚባለው ቀድሞ አዳም የሠራው ኋላም አብርሃምና ልጁ እስማኤል ያደሱት ሳይሆን ለብዙ ዘመናት የአረማውያን መቅደስ ብቻ ነበር:: አሁንም መሐመድ ከመካ ጣዖት አምላኪዎች ጋር የነበረውን ምልልስ እንመልከት:-

*«ይልቁንም /የመካ ከሐዲዎች/ የፊተኞቹ ሕዝቦች እንዳሉት ብጤ አሉ . . . ምድርና በውስጥዋ ያለው ሁሉ የማን ነው? የምታውቁት ብትሆኑ ንገሩኝ /በላቸው/ በርግጥ የአላህ ነው ይሉሃል ታዲያ አትገሠጹምን? /በላቸው/ »* /ሱረቱ 23÷81-89/



www.ethiopianorthodox.org

ገና በክህደታቸው ላይ ስለጸኑ የሚገሰጹትን የመካን ከሃዲዎች ስማሃቸው? ምድርና በውስጧ ያለው የማን ነው ተብለው ሲጠየቁ አናውቅም አላሉም የሚያውቁትን ስም አላህን ይጠሩ ነበር:: ለመካ ከሃዲዎች /ጣዖት አምላኪዎች/ አላህ አዲስ ቢሆን ኖሮ አላህ ምን ማለት እንደሆነና እርሱ ማን እንደሆነ በጠየቁ ነበር ነገር ግን መሐመድ ከመካ ጣዖት አምላኪዎች ላይ ማስረቀት የፈለገው የለመዱትን ታላቁን ጣዖት አላህን ሳይሆን አሁን በጠቀስነው ምዕራፍ 23 ቀጣዮቹ አንቀጾች 90 እና 91 ላይ:-

*«ይልቁንም እውነትን አመጣንላቸው እነርሱም /በመካዳቸው/ ውሸታሞች ናቸው:: አላህ ምንም ልጅን አልያዘም /አልወለደም/ ከርሱም ጋር አንድም አምላክ የለም ያን ጊዜ /ሌላ አምላክ በነበረ/ አምላክ ሁሉ በፈጠረው ነገር በተለየ ነበር ከፊላቸውም በከፊሉ ላይ በላቀ ነበር አላህ ከሚመጥኑት ሁሉ ጠራ»*

በማለት እንደገለጸው እርሱ ያመጣው አዲስ እውቀት ቢኖር አላህ ልጅ ያዘ /ወለደ/ ከማለት እንዲከለከሉ ብቻ መሆኑን አስረዳቸው:: የመካ ከሃዲዎች የሚያውቁት የጨረቃው አምላክ አላህ ከፀሐይ አምላክ ጋር ተጋብቶ ሦስት ልጆች የወለደ ነው እነዚህም ልጆቹ ቁርአን ላይ ተጠቅሰዋል:-

*«አል-ላትንና አል-ዑዛን አያችሁን? ሦስተኛይቱንም አነስተኛዋን መናትን አያችሁን? የምትገዟቸው ኃይል አላቸውን? ለናንተ ወንድ ለርሱም ሴት /ልጅ/ ይኖራልን?»* (ሱረቱ 53÷19-21)

«ለእርሱ» የተባለው አላህ ሲሆን ሦስት ልጆቹ ናቸው ተብሎ መታመኑ በቁርአኑ በግልጽ ተቀምጧል አላህ በበጋ ከአል-ላት



በክረምት ደግሞ ከአል-ዑዛ ጋር ይኖራል ተብሎም ይታመን ነበር:: ተጨማሪ ጥቅሶችን እንይ:-

*«የመካን ሰዎች/ ጠይቃቸውም ለጌታህ ሴቶች ልጆች ለነርሱም ወንዶች ልጆች ይኖራልን?»* /ሱ. 37÷149/

*«ለአላህም /ከመላእክት/ ሴቶች ልጆችን ያደርጋሉ ጥራት ተገባው ለነርሱም የሚፈልጉትን/ ወንዶች ልጆችን/ ያደርጋሉ»*

/ሱረቱ 16÷57/

አንባቢ ሆይ! አሁንስ ግልጽ አይደለም? አላህም ከሚመጥኑት ጠራ በማለት ከፀሐይ አምላክ ከሦስቱ ልጆቹ በአጠቃላይ ከሚመጥኑት ጣዖታት ሁሉ ጠርቶ /ተለይቶ/ ብጤ የሌለው ተብሎ እንዲመለክ መሐመድ አወጀ:: መሐመድ በሰማው የአንድ አምላክ አምልኮ መሠረት አላህን ብቻ ተገዙ ብሎ ሲመጣ ለመካዎች የቀለለውን ያህል አይሁዶችና ክርስቲያኖች ባለመቀበላቸው ብዙ መከራ ተቀብለዋል::

የአላህ አምልኮ ብቻ ሳይሆን አላህ ወደ ሚገኝበት ወደ መካ /በመካ ወደ ሚገኘው ካዕባ ሐጅ /ጉዞ/ ማድረግም ከመሐመድ መነሳት በፊት ለዘመናት የቆየ አረማዊ ልማድ ነው:: የመሐመድን ታሪክ የሚናገረው ዘግሬት ላይት የተሰኘው መጽሐፍ እንዲህ ይላል:-

«በስምንተኛው ዓመተ ሒጅራ ሐጅ ለማድረግ ወደ መካ ለመሄድ ወሰኑ ሙስሊሞችንም ለሐጅ ሥነ ሥርዓት እንዲዘጋጁ ነገሯቸው ሙስሊሞች ሁሉ ተደሰቱ በተለይም ሙሐጂሮች (ከመካ ወደ መዲና የተሰደዱት) ምክንያቱም ለሐጅ ወደ መካ መሄድ ማለት ለነርሱ ወደ አገራቸው ቤተሰቦቻቸውና ወደ አደጉበት ምድር መምጣት ስለሆነ ነው ቁረይሾች የአላህን መልክተኛ ውሳኔ ሲሰሙ ፍርሀት ያዛቸው ምክንያቱም ሙስሊሞች በዚያን ሰዓት ጠንካሮች ስለሆኑ ነው ጊዘው



www.ethiopianorthodox.org

ይህም ለመጽሐፉ ሰዎች የተሰጠ ማስጠንቀቂያና የሞት አዋጅ ነው:: በቁርአን የቅርቢቱ ዓለምና የመጨረሻይቱ ዓለም የሚባሉ ዓለማት አሉ እስልምናን ያልተቀበሉና በአላህ ያላመኑ የመጨረሻይቱ ዓለም ዕድል ፈንታ እንደሌላቸውና የእሳት ጓዶች እንደሆኑ የተገለጠ ሲሆን በቅርቢቱ ዓለም ማለትም በዚህች ዓለም ሕይወታቸው ግን ቅምጥሎችና ደስተኞች እንደሆኑ ተዘግቧል::

*«የነዚያን የካዱትን ሰዎች በአገሮች መንፈላሰስ አያታልልህ አነስተኛ ጥቅም ነው ከዚያም መኖሪያቸው ገሀነም ናት ምን ትከፋም ምንጣፍ»* (196-197፡ 145)

ነገር ግን የመጽሐፉ ሰዎች እስልምናን ባለመቀበላቸው ብቻ ከሃዲዎች የሚያገኙትን የቅርቢቱን ዓለም ሕይወት እንኳ ተከልክለዋል ለነርሱ በተገኙበት ስፍራ ለዝርፊያና ግድያ ተሰጥተዋል ይህ አንቀጽ ለብዙ አይሁዶችና ክርስቲያኖች ስደት መከራና ሞት ምክንያት ሆኗል በተገኙበት ቦታ ንብረታቸው ይዘረፋል ቤታቸው ይቃጠላል ሚስቶቻቸውንና ሴቶች ልጆቻቸውን ሲቀሙ ወንዶቹ የሰይፍ እራት ሆነዋል ግን ለምን? በክርስቲያኖች መሃል የሚኖር አንድ ሙስሊም ተከብሮ በፍቅር ሊኖር እንደሚችል ማንም የማይክደው ሃቅ ሲሆን ሙስሊሞች በበዙበት አካባቢ/ አገርና መንግሥት የሚኖሩ ጥቂት ክርስቲያኖች የሚደርስባቸው ግፍና ጭካኔ የተሞላው ድርጊት ትናንት ብቻ ሳይሆን ዛሬም በግልጽ እየታየ ያለ እውነት ነው:: እዚህ ላይ በመጽሐፉ ሰዎች ላይ አስቃቂ አደጋ ለማድረስ ሁሌ የሚቀርብ ክስ አለ የመጀመሪያው:-

- በአላህ ተአምራት ስለከዱ የሚል ሲሆን ሁለተኛው



- ነቢያትን ያለ ሕግ ስለገደሉና ወሰንን በማለፋቸው ወዘተ የሚሉ ክሶች ይሰማሉ

የአላህ ተአምራት የተባለው ቁርአን ነው ለማያነብ ለማይጽፍ መሐመድ በመውረዱ ብቻ ተአምር ይባላል ቁርአን ከሚደግማቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቀድሞ የተዘገቡ ታላላቅ ተአምራት በቀር በቁርአን ውስጥ አላህ የፈጸመው ተአምር የለም በመሐመድም የተፈፀመ ተአምር አለመኖሩ ግልጽ ነው:: ቢሆንም ቁርአንን አለመቀበል የአላህን ተአምር እንደመካድ ተቆጥሯል በሌላ መልኩ ማንም ሊያደርጋቸው የማይችላቸው ታላላቅ ተአምራት በኢየሱስ ክርስቶስ መፈጸማቸው እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ ቁርአኑም ማረጋገጡን አስቀድመን በሰፊው ተመልክተናል:: ሌሎችም ቁርአን በመጽሐፉ ሰዎች የሚያነሳቸው ክሶች ጠቅላላ ፈጽሞ ከእውነት የራቁ ውስጣዊ ጥላቻን ማንጸባረቂያ ብቻ ናቸው:: ሰዎችን ለማዳን ጥቂት መልካምነትን መፈለግ የአምላክ ባሕርይ ሲሆን ሰዎችን ለማጥፋት ኃጢአት /ክስ/ ማብዛት ግን የሰይጣን ሥራ ነው:: ለመሆኑ እነዚህ ሁሉ በመጽሐፉ ሰዎች ላይ ቁርአን የሚያነሳቸው ክሶች ከቁርአን መውረድ በፊት በ7ኛው ሰማይ ተጽፈው ተቀምጠው ነበርን? ወይስ ችግሮች ናቸው ባለ በመሐመድ የተጨመሩ?

የነቢያት ታሪክ የሚያያዘው ከቤተ እስራኤል ጋር ሲሆን በመካከላቸው የሐሰት ነቢያትም ስለሚኖሩ እነዚህ ለእግዚአብሔር ነቢያት መገደል ምክንያት ይሆናሉ ነገር ግን አይሁድ የነቢያት ሁሉ ትንቢት ፈፃሚ የሆነውንና ራሳቸው ይጠብቁት የነበረውን መሢሕ /ክርስቶስን/ ስቅለትና ሞት ከ600 ዓመት በኋላ የተነሣው መሐመድ አልሰቀሉትም አልገደሉትም ብሎ አስተባበለላቸው ነቢያትን ገደሉ



www.ethiopianorthodox.org

የብርሃን ዘውድ አምላክ እንደሚደፋልን ካሰብን እርሱ አምላክ አይደለም ትዕግስት ያለቦታው ዋጋ አያስጥም ያለ ኃጢአት ሲጐስም የታገስ ለጠላቶቹም ምሕረት የለመነ በፍቅርም የሞተ እርሱ ኢየሱስ ነው እርሱም የዓለም መድኃኒት ሆኗል ያለ ኃጢአት ለኃጢአተኞች የከፈለውን ዋጋ የሚቀበሉ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉ ልጅነታችን ለመንግሥቱ ያበቃናል ሰው በዚህ ንጹሕ እምነት ላይ ቆሞ መከራን ቢቀበል ቢታገስም ታላቅን ክብር ይቀበላል /ዕብ. 12-1-2/ ኤልያስን ሲቃወሙ የነበሩ የበአል /የጣዖት/ ካህናትና ነቢያት ጣዖቱ እንዲሰማቸው ማሽብሸባቸው አልበቃ ብሏቸው ሰውነታቸውን በቢላ እየተለተሉ ደም እስኪያስክራቸው ይጮሁ ነበር ዋጋ አልባ መስዋእትነት ከፈሉ በንጹሕ ሃይማኖት የሆነውን የኤልያስን ልመና ግን አምላክ በቅጽበት ሲመልስ መስዋዕቱንም ሲቀበል አስተውለናል /1ነገ. 18፥25-40/ ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች በውስጡም ድንግል የሆኑ ሴቶችን እያሰበ እንዲዋጋ የዋህ የሆነን ሰው ሊያበረታታ ይችል እንደሆነ እንጂ ውጊያ የገነት ቁልፍ ሊሆን አይችልም የመጀመሪያው ሰው በሰይጣን ተታሎ ከገነት በኃጢአት ምክንያት ተባረረ የዚህ ሰው ልጅ ደግሞ ወንድሙን ገደለ ተታሎ ኃጢአት የሠራው ሰው ሆነ ብሎ ኃጢአት መሥራት ጀመረ መግደል አትግደል የሚለውን ሕግ የተላለፈ የድፍረት ኃጢአት ነው ዳዊት ዘመኑ የጦርነት ዘመን ስለነበረ የእግዚአብሔርን መቅደስ እንዳይሠራ ተከለከለ ኋላም ኦርዮንንም ስላስገደለ ከዙፋኑ ተሰደደ (2ሳሙ 7፥1-17፣ 11፥1-27፣ 12፥1-15)

በዚህ አንቀጽ መሠረት ብዙዎች መሞትን ይፈልጉ እንደነበርና ጦርነቱ ሲመጣ ግን እንደሸሹ በአንቀጽ 143 ላይ የተገለፀ ሲሆን



ከመሐመድ አፍ ቁርአኑን በቃላቸው አጥንተው ሊቃውንት የተባሉትም ብዙዎች ጦርነት ላይ እንደተሰለፉ አንቀጽ 146 ላይ ተገልጿል በእነዚህ አንቀጾች ውስጥ መሞት ወይም መገደል ይላል እንጂ መግደል አይልም ነገር ግን የገነት ቃል ኪዳን በመገደል ብቻ ሳይሆን በጭካኔ በመግደል እንደሚረጋገጥ በቀጣዩ አንቀጽ 152 ላይ ተገልጿል።

*«አላህም በፈቃዱ በመትጨፈጭፏቸው ጊዜ ኪዳኑን በእርግጥ አረጋጋጠላችሁ የምትወዱትንም ነገር ካሳያችሁ በኋላ በፈራችሁ በትእዛዙም በተጨቃጨቃችሁና ባመጣችሁ ጊዜ /እርዳታውን ከለከላችሁ/ ከናንተ ውስጥ ቅርቢቱን አለም የሚሻ አለ የመጨረሻይቱን ዓለም የሚሻ አለ ከዚያም ሊሞክራችሁ ከነሱ አዞራችሁ በእርግጥም ከናንተ ይቅርታ አደረገላችሁ አላህም በምእመናን ላይ የችሮታ ባለቤት ነው።»*

በአንቀጽ 151 ላይ የአጋሪዎች /ብዙ አማልክት የሚያመልኩ/ መኖሪያ እሳት መሆኗን ይናገራል ይህ እንግዲህ በነፍስ ነው። እነዚህ በነፍስ ብቻ ሳይሆን በዚህ ዓለም ሲኖሩም ለመጨፍጨፍ የተሰጡ ናቸው ምእመናኑም /ሙስሊሞቹ/ እነዚህን በመጨፍጨፋቸው የገነት ኪዳን ይረጋገጥላቸዋል። እግዚአብሔር ፍቅር ነው ሁሉን በፍቅር ፈጠረ ብሎ የሚያምን ሁሉ የፍቅር ፍጥረቱን በፍቅር አይን ማየት ካልቻለ እርሱ ከእግዚአብሔር አይደለም።

*«እግዚአብሔር ፍቅር ነው በፍቅርም የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል»* /1ዮሐ 4፥16/

ያላመነም ሰው አላማመኑ የእግዚአብሔርን ታማኝነት አያስቀርም እግዚአብሔር በፍቅሩ ታማኝ ስለሆነ ያልወደደውን እንኳ ሊጠላ



www.ethiopianorthodox.org

አይችልም አንተ ታዲያ ባለቤቱ ያልጠላውን ለርሱ ብለህ ለምን ትጠላላህ? ፍቅርም ያለ ምንም መመዘኛ መውደድ ነው ሃይማኖት እንኳን ለመጨፍጨፍ ለመውደድም ምክንያት ሊሆን አይገባውም የአምላክ ፍቅር እንዲሁና ዘላለማዊ ነው /ዮሐ. 3÷16፣ ኤፌ 2÷5/ ዲያብሎስ ግን ነፍሰ ገዳይ ነው፡-

*«እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበር.»* /ዮሐ. 8÷44/

## 33. ሰለባን የሚቀበለው ነቢይ

## አንቀጽ 161

*«ለነቢይም ሰለባን መደበቅ አይገባውም ሰለባን የሚደብቅ ሰው በትንሣኤ ቀን በደበቀው ነገር /ተሸክሞ/ ይመጣል ከዚያም ነፍስ ሁሉ የሥራዋን ዋጋ ትመላለች እርሱም አይበደሉም።»*

መሐመድ ከመካ በተለየ ሁኔታ በመዲና የጦር መሪ ስለነበረ እጅግ ዘግናኝና ጭካኔ የተመላባቸው ርምጃዎችን ባለሙኑት ላይ ይወስድ ነበር ከዚያም ውጭ ባሎች የሞቱባቸው ብዙ ሴቶች ማግባት ካልፈለጉ ተከብረው የሚኖሩ ማግባትም ከፈለጉ መርጠው የሚየገቡ አልነበሩም ያላቸው አማራጭ የመሐመድ ሚስት ወይም ቁባት የመሆን ግዴታ ብቻ ነበር። አይቶ የወደዳትን ሴት ከባሏ ሥር ለመውሰድ ከልካይ የለውም ለምሳሌ መሐመድ የ6 ዓመቷን አይሻን ባጫት በ3ተኛ ዓመት 9 ዓመት ሲሆናት አግብቷታል ያኔ እርሱ 53 ዓመቱ ነበር የጉዲፈቻ ልጁን ሚስትም ነጥቆ ማግባቱን ይታወቃል።



እስልምናን ያልተቀበሉ ወይም የተቃወሙ ሰዎች ብዙ ዓይነት ቅጣት ይደርስባቸው ነበር፡-

«የነዚያ አላህንና መልክተኛውን የሚዋጉ በምድርም ላይ ለማጥፋት የሚተጉ ሰዎች ቅጣት መገደል ወይም መሰቀል ወይም እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን በማፈራረቅ መቆረጥ ወይም ከአገር መባረር ነው ይህ ለነርሱ በቅርቢቱ ዓለም ውርደት ነው በመጨረሻይቱም ለነርሱ ከባድ ቅጣት አላቸው» (አል. ማኢዳህ 5÷33)

እነዚህ መሐመድ በሚቃወሙት አለበለዚያም በጦርነት በማረካቸው ላይ የሚያደርሳቸው ጭካኔ የተሞላባቸው ቅጣቶች ናቸው። በዚህ መልኩ ቅጣት የተወሰነባቸው ሰዎች በሕይወት ሳሉ ወይም ከሞቱ በኋላ ይሰለቡ ነበር። የተሰለቡ ሰዎች በሕይወት እንኳ ቢኖሩም ዳግመኛ ማግባትና መውለድ እንደማይችሉ ይታወቃል። አንቀጹ እንደሚለው መሐመድ የሰለባችሁትን ለኔ አትደብቁ በማለት ያስጠነቅቃል ምክንያቱም ማርከው ወይም ገድለው በሰለቡት ልክ ሽልማት ስልጣን ለመስጠት በዚህም የበለጠ እንዲጋደሉ ለማበረታታት ነው። ደግሞ ሕጉን መንፈሳዊ ይዘት ለመስጠት የሚደብቅ ሰው በትንሣኤ ቀን በደበቀው ነገር /ተሸክሞ/ ይመጣል በማለት ከፍርድ ቀን ጋር አያያዘው በማይሞት ሕያው አካል በምድር በኖርንበት ማንነት ተለይተን የምንነሳበትን ቀን ሰው የቀማውን የሰረቀውንና የሸሸገውን ተሸክሞ የሚመጣበት ቀን አደረገው ማን ምን እንደሆነ / እንደሠራ/ አምላክ ስለማያውቅ ይሆን ተሸክሞ መምጣት ያስፈለገው? ይህም ከሰማይ የወረደ ነው ተብሎ ይነበባልን? አምላክ ካልረዳ ማን ያስተውላል?



www.ethiopianorthodox.org

አንቀጽ ጋር ተመሳሳይ መልእክት የያዙ አንቀጾች በዚህ ምዕራፍ እንኳ ማግኘት የሚቻል ሲሆን ለሐበሻ ንጉሥ ተሰጥተው አለመተርጐማቸውን እናያለን:: ለምሳሌ በዚሁ ምዕራፍ አንቀጽ 110 እና 119 ላይ =

*«... የመጽሐፉም ሰዎች በአመኑ ኖሮ ለእነርሱ የተሻለ በሆነ ነበር ከእነርሱ አማኞች አሉ አብዛኞቻቸው ግን አመፀኞች ናቸው»*

*«(የመጽሐፉ ሰዎች ሁሉ) እኩል አይደሉም ከመጽሐፉ ሰዎች ቀጥ ያሉ በሌሊት ሰዓቶች እነርሱ የሚሰግዱ ሆነው የአላህን አንቀጾች የሚያነቡ ሕዝቦች አሉ»*

እነዚህ አንቀጾች ለምን ለሐበሻ ንጉሥ አልተሰጡም? በቁርአኑ ውስጥ እንኳ ያልተጠቀሰው ታሪክ በግርጌ ማስታወሻ ከጊዜ በኋላ መጨመሩ ለሌለ ታሪክ እውቅና ለመስጠት የተደረገ ሙከራ ቢሆንም ብዙ አያስኬድም::

ለመሆኑ የንጉሡ ስም ማን ነው? በግርጌው ማስታወሻ የአብደላ ሰላም ስም ሲጠቀስ የሐበሻው ንጉሥ ስም አለመጠቀሱ በንጉሡ ማንነት ላይ ርግጠኛ መረጃ እንደሌላቸው በቂ ማሳያ ሲሆን አሁን ግን ይህ ንጉሥ አልነጋሺ እንደሚባልና እርሱም አክሱም ላይ በ7ተኛው ክ/ዘመን የነገሠና እስልምናን የተቀበለ መሆኑ በሰፊው እየተዘገበ ይገኛል::

በ615 ዓ.ም የመሐመድ ተከታዮች ከመካ ተሰደው ነፍሳቸውን ለማዳን ወደ ኢትዮጵያ በተሰደዱ ጊዜ አክሱም ላይ የነበረው ንጉሥ ማን ነው? ሙስሊም ወገኖቻችን አልነጋሺ ነው የሚሉን ከሆነ -



1- አልነጋሺ የሚባል ንጉሥ በኢትዮጵያ ምድር ከነገሡ ነገሥታት ስም ዝርዝር ውስጥ እስከዛሬ አለመገኘቱ አባባሉን ትርጉም የለሽ ያደርገዋል ከ550 - 1270 ዓ.ም ድረስ በኢትዮጵያ የተመዘገበ የታሪክ ማስረጃ የለም የሚል አደናጋሪ መግለጫ መስጠቱ ማረጋገጫ ለሌለው ታሪክ ሽፋን ሊሆን አይችልም:: ከታሪክ ጸሐፊዎች በተጨማሪ ቤተ ክርስቲያን የሀገርና የታሪክ ባለአደራ ስለሆነች ይህን ዘመን በብዙ ታላላቅ መንፈሣዊ ክንዋኔዎች ስለምትዘክር በቂ መረጃ አላት::

2- ዐረቡ ምድር ላይ የነበሩ አይሁዶችና ክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆኑ የመካ ጣኦት አምላኪዎች እንኳ ያልተቀበሉትን የመሐመድ ትምህርት የብዙ ዘመን ጠንካራ የክርስትና ታሪክና ባህል ያለው የአክሱም መንግሥት ተቀበለ ብሎ ማሰብ እንዴት ይቻላል:: አክሱምስ የእስልምና መናገሻ ሆና ይሆን?

3- የመሐመድ ተከታዮችስ ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ሃይማኖት ያለው ደግ ንጉሥ አለ እርሱ አሳልፎ አይሰጣችሁምና ወደ እርሱ ሄዳችሁ ነፍሳችሁን አድኑ ተብለው ነው ወይስ ሃይማኖት የለሽ ንጉሥ አለና ሄዳችሁ ሰብካችሁ አሳምኑ ተብለው?

«አክሱም» የተሰኘው መጽሐፍ ስደተኞቹን በተመለከተ መሐመድ ያስተላለፈውን መልእክትና ከዚያም በኋላ የተፈጸመውን ታሪክ እንዲህ በማለት ያስቀምጣል::

«ራሳችንን ለመከላከል አላህ ብርታቱን እስኪሰጠን ድረስ ወደ ሐበሻ አገር ሄዳችሁ ቆዩ በእርስዋ አንድ ንጉሥ አለ እርሱ



www.ethiopianorthodox.org

ይህን አመለካከት አንድ የታሪክ ምሁር «ብዙ ተከታይ ከአካባቢውና ከጐረቤት አገሮች ለማግኘት የተደረገ ጥረት» ሲሉት (ስርግው፥ 190) ኮቢሻኖቭ የተባለው የታሪክ ሰው ከመሐመድ ለንጉሡ ተጻፈ የተባለውን ደብዳቤ በተመለከተ «የፈጠራ ወሬ» ብሎታል (Axum፥ 112) እንዲሁም ተክለ ጻድቅ መኩሪያ «የዚህን የወዳጅነት ግንኙነት በክርስቲያኑ አክሱማዊ ንጉሥና እስልምናን በመሠረተው በመሐመድ መካከል የተደረገውን የደብዳቤና የሰላምታ መተዋወቅ የሚያውቁ የዐረብ ጸሐፊዎች የአክሱም ንጉሥ የሰለመ መስሏቸው ጽፈው እንደሆነ አይታወቅም» በማለት ገልጸዋል:: (የኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ አክሱም ዛጉዬ፥ 376) ስለዚህ ይህና ሌሎች የታሪክ ሰነዶች እንደሚያስረዱት አልነጋሺ የሚባል ንጉሥና እስልምናን የተቀበለ የአክሱም መንግስት አለመኖሩን በመገንዘብ ታሪክ እንዳይዛባ ሁላችንም ልንጠነቀቅ ግድ ይለናል::

አንባቢ ሆይ! እግዚአብሔር ሕይወትን እስከዚህ ሰዓት የጠበቀው እጅግ ስለሚወድህ ሲሆን ፍቅሩ ገብቶህ ከጥፋት መዳንህ የዘላለም ዓላማው ነው:: ስለዚህ ለምን ትዘገያለህ? መሠረትህ ሌላ ከሆነ ቶሎ አምልጥ መሠረቱ ላይ ካለህ ደግሞ በንስሐ ተደላደል::

> «ንቁ በሃይማኖት ቁሙ ጐልምሱ ጠንክሩ በእናንተ ዘንድ ሁሉ በፍቅር ይሁን» (1ቆሮ. 16፥3)

ለእግዚአብሐር ክብር ምስጋና ይሁን!!

ይቆየን!!



## ዋቢ መጻሕፍት


1. መጽሐፍ ቅዱስ (ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን) ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት, 1962
2. ቁርአን (አማርኛ ትርጉም) ነጃሺ አሳታሚ, 1961
3. በውኑ በኢትዮጵያ የሃይማኖት መቻቻል አለን? አባ ሳሙኤል (ጳጳስ) አዲስ አበባ 2000፣ ዓ.ም.
4. አብዱልመሊክ ዓሊ አልኩለይካ የፈጣሪ አንድነት በአራት በወንጌልና በቁርአን ትርጉም ኢብራሂም ነጃሺ አሣታሚ
5. በላይ ግደይ አምሐ (1995) አክሱም፣አዲስ አበባ
6. ተክለ ጻድቅ መኩሪያ (1958) የኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ አክሱም ዛጉዬ 1ኛ መጽሐፍ አ.አ.
7. አቡ ያሲር አብዱልመናን አልገላይኒ (2000) The great Light አ.አ.
8. Sergew Hable Sellassie (1977), Ancient and Medieval Ethiopian History to 1770; A.A
9. Yuri M.Kobishanov (1979), Axum, Joseph W.Michus (trans), Pennsylvania state Univerisity Press.




www.ethiopianorthodox.org

በቀጣዩ ቴቄል ክፍል ሦስት ላይ
ሥላሴን በተመለከተ በእስልምና ያለውን የቁርዓን
አስተምህሮ በሰፊው እንመለከታለን
በቅርብ ቀን ይጠብቋት



ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለም ያው ነው።

ዕብ 13፥8

የእግዚአብሔርም ልጅ እንደመጣ እውነተኛ የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደሰጠን እናውቃለን እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ እውነተኛ አምላክ እና የዘላለም ሕይወት ነው። ልጆች ሆይ እራሳችሁን ከጣዖታት እርሳቹን ጠብቁ።

1ኛ ዮሐ 5፥20-21

<u>ከዚህ ቀደም የታተመ</u>

- ቴቄል ክፍል አንድ

<u>በቅርቡ የሚታተሙ</u>

- ቴቄል ክፍል ሦስት
- የእስልምናና የክርስትና መሰረታዊ ልዩነቶች

በየመጻሕፍት መደብሩ ያገኙታል ዛሬውኑ ይያዙት

ዋጋ 12 ብር

www.ethiopianorthodox.org